## አራተኛ ቀን

### አራት የተለያዩ ተግባራትንና እነዚህ ተግባራት ለጊዜ አጠቃቀማችን የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ መረዳት::

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በየቀኑ ብዙ ሥራዎች ያጋጥሙታል:: ከዚህ በታች ካለው ሠንጠረዥ ውስጥ አራት ተ ግባራትን ተመልከት::

| | |
|---|---|
| **አስቸኳይና አስፈላጊ ተግባራት:-**<br>በቤተ ክርሰቲያን ውስጥ የሚፈጠር ችግር (ለምሳሌ፣ የሰው መሞት)<br>መፍትሔ ማግኘት ያለባቸው ጉዳዮች (ምሳሌ፣ የመሪዎች መጣላት)<br>ቀጠሮ (ለምሳሌ፣ ሪፖርቶች፣ ፕሮጀክቶች) | **አስቸኳይ ያልሆኑና ዳሩ ግን አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት:-**<br>ሰዎች እንዲያድጉ መርዳት (ለምላሴ፣ ሰዎችን ማስተማርና ማሠልጠን)<br>ግንኙነቶችን መገንባት (ለምላሴ፣ ከልጆች፣ ከሚስት፣ ከሽማግሌ ዎች ጋር)<br>አዳዲስ የአገልግሎት ዕድሎችን ማግኘት |
| **አስቸኳይና ዳሩ ግን አስፈላጊ ያልሆኑ ተግባራት:-**<br>የሚያቋርጡ ነገሮች (ለምላሴ፣ የስልክ ጥሪ፣ የጓደኞች ንግግር)<br>አንዳንድ ደብዳቤዎችና ሪፖርቶች<br>አንዳንድ ሰብሰባዎች | **አስቸኳይም አስፈላጊም ያልሆኑ ተግባራት:-**<br>የኮምፒዩተር ጌም መጫወት<br>ጋዜጣ ወይም መጽሔት ማንበብ<br>ከጓደኛ ጋር መጫወት |

**1. አስቸኳይና አስፈላጊ** ተግባራት:- እነዚህ በድንገት የሚከሰቱና በፍጥነት መከናወን ያለባቸው ነገሮች ናቸው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ በፍጥነት ሄደን ቤተሰቡን ልንጎበኝና የቀብር ሥነ-ሥርዓት ልናዘጋጅ ይገባል:: ሞት መቼ እንደሚመጣ መተንበይ አይቻልም:: ከተከሰተ በኋላ በፍጥነት አለመሄድ ደግሞ ሰዎች ለሰው ፍቅር እንደሌለን አድርገው እንዲያስቡ ያደርጋል:: ወይም ደግሞ ባልና ሚስት እየተጣሉ ይሆናል:: በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ላይ ጉዳት ከመድረሉ በፊት በፍጥነት ሄደን እርቅ ማውረድ አለብን:: ወይም ደግሞ ሪፖርቱን



ሳናጠናቅቅ ነገ የቦርድ ስብሰባ ሊካሄ ነው:: ከስብሰባው በፊት ሪ ፖርቱን ማጠናቀቅ እንድንችል አሁኑኑ በሪፖርቱ ላይ መሥራት አለብን::

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እነዚህን ተግባራት በተመለከተ ምን ማድረግ አለበት?

<u>በመጀመሪያ</u>፣ መሪ አስቸኳይና አስፈላጊ ለሆኑት ነገሮች አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት አለበት:: መሪ ለየትኛውም የጊዜ ሠሌ ዳ ባሪያ አይደለም:: ሁላችንም በእግዚአብሔር ጊዜ ሠሌዳ ቁጥጥር ሥር ነን:: የእርሱን የጊዜ ሠሌዳ አሰቀድመን ልናውቅ አንችልም:: እግዚአብሔር የሚወስናቸውና መሪው የማያውቃቸው ነገሮች አሉ:: እንደ ሞት ወይም የሆነ ሰው ለአስፈላጊ ጉዳይ እኛን ለማግኘ ት የሚመጣበትን ሁኔታ የሚመስሉ ነገሮች ይከሰታሉ:: መንፈሳዊ መሪ ሁልጊዜም ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት አእምሮውን ክፍት ያደርጋል:: ስለሆነም፣ መሪው ለእነዚህ ነገሮች ምላሽ ለመስጠት እንዲችል ሁልጊዜም ዕቅዶቹን ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆን አለበት:: ያዘኑ ቤተሰቦችን ማጽናናት ወይም የተጣሉ ሰዎችን ማስታረቅ አለበት::

<u>ሁለተኛ</u>፣ መሪው የሚያጋጥሙትን አስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳዮች ቁጥር ለመወሰን ጥረት ማድረግ አለበት:: ይህንንም የሚያደርገው ሁኔታዎች አስከፊ ገጽታ ከመያዛቸው በፊት ፈጥኖ መፈትሔ በማፈላለግ ነው:: ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጸብ መጀመሩን ከሰማ፣ በፍጥነት መጋቢው ሰዎቹን እንዲያነጋግራቸው ማድረግ አለበት:: ይህ ጉዳዩ አስቸኳይና አስፈላጊ እንዳይሆን ያደርገዋል:: የቦርድ ስብሰባው ነገ ሊካሄድ ዛሬ በሪፖርቱ ላይ እንዳይጠመድ ደግሞ ቀደም ብሎ ሊያዘጋጀው ይችላል:: ቀደም ብሎ ሪፖርቱን ከሠራው፣ ብዙ ችግሮች ይወገዳሉ:: ይህ ሪፖርቱ አስቸኳይና አስፈላጊ እንዳይሆን ያደርገዋል::

> 32ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም መጋቢ የሚጋፈጠውንና በፍጥነት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባውን አስቸኳይና አስፈላጊ ነገር ግለጽ:: ለ) ይህ ሁኔታ እንዳይከሰት መከላከል የሚቻልበት መንገድ ነበር?

**2. አስቸኳይ ያልሆኑ አስፈላጊ** ተግባራት:- እነዚህ እንደ መሪ ዎች የሚያጋጥሙን እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: እነዚህ ነገሮች አስፈላጊዎች በመሆናቸው እንደ መሪዎች ውጤታማ መሆን አለመሆናችንን የመወሰን አቅም አላቸው:: ነገር ግን እነዚህ ነገሮች አስቸኳይ ባለመሆናቸው ጠንቃቃ ካልሆን፣ ሳናተኩርባቸው ልንቀር እንችላለን:: እነዚህ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን እድገት እንድናዘጋጅ የሚፈልጋቸው እንደ ራእይና ዕቅዶች ያሉትን የሚመለከቱ ናቸው:: አስቸኳይ ያልሆኑ አስፈላጊ ተግባራት ከሚያካትቷቸው ነገሮች መካከል የተሻለ የአገልግሎት ግንኙነት ይኖረን ዘንድ ከሌሎች ሽማግሌዎች ወይም አገልጋዮች ጋር መልካም ግንኙነትን መመሥረት፣ አገልግሎታችንን በተሻለ መንገድ ለማካሄድ እንድንችል ትምህርት ወይም ሥልጠና መውሰድ፣ ውክልና እንስጣቸው ዘንድ ሰዎችን ማሠልጠን፣ የግን ኙነት ችግሮች እንዳይፈጠሩ በማሰብ ምእመናን እንዴት በሰላምና በፍቅር ሊኖሩ እንደሚችሉ ማስተማር፣ ሁልጊዜም ነገሮችን ስለምናከናውንበት ሁኔታ ጥርጣሬ እንዳይኖራቸው መሪዎችና ምእመናን በእኛ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ተ ግባራትን ማከናወን ይገኙባቸዋል::

መሪዎች በእንዲህ ዓይነት ነገሮች ላይ ብዙ ጊዜ ባሳለፉ ቁጥር፣ «አስቸኳይና አስፈላጊ» ወይም «አስቸኳይና አስፈላጊ ባልሆኑ ነገሮች» ላይ የመሳተፍ ዕድላቸው ይቀንሳል:: ለምሳሌ፣ አንድ መሪ አማኞች እንዴት በሰላምና በስምምነት ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚያስተምር ከሆነ፣ በአስቸኳይ መፍታት ያለብን የግንኙነት ችግሮች እምብዛም ላይከሰቱ ይችላሉ:: ወይም ደግሞ አንድ ሰው ጥቃቅን የሆኑትን የቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉዳዮች እንዲከታተል ብንመድበው፣ በእኛ የአመራር ደረጃ መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ለማከናወን ጊዜያችንን ልንጠቀም እንችላለን::

እውነተኛው የአመራር ሥራ የሚሆነው «አስቸኳይ ያልሆኑትንና አስፈላጊ ተግባራትን» ማከናወን ነው:: እግዚአብሔር እንደ ቤተ ክርስቲያን ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ ለመረዳት በመጣርና ይህንኑ ራእይ እውን ለማድረግ የሚያስችሉትን ዕቅዶች



በመንደፍ፣ ወይም ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ያካሂዱ ዘንድ በማሠልጠን፣ ወይም ሰዎች እንዴት መንፈሳዊ ሕይወት እንደሚኖሩና ወንጌሉን እንደሚያካፍሉ በማሠልጠን ጊዜያችንን በምናሳልፍበት ጊዜ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ እድገት ይካሄዳል::

ግንኙነቶችን መመሥረት «አስቸኳይ ያልሆነና አስፈላጊ የሆነ ተግባር» በመሆኑ፣ አስተዋይ መሪዎች ጊዜያቸውን ግንኙ ነቶችን በመገንባት ላይ ያሳልፋሉ:: አስተዋይ መሪዎች ግንኙነቶቻ ቸው በሙሉ አስፈላጊዎች መሆናቸውን ስለሚረዱ፣ የጊዜ አጠቃቀማቸውን ግንኙነቶቻቸውን ከመጠበቅ ጋር ሚዛናዊ ያደርጋሉ:: ቤተሰቦቻቸውን በሚገባ ካልተንከባከቡ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ሊመሩ እንደማይችሉ ስለሚያውቁ፣ ለቤተ ሰቦቻቸው ጊዜ ይሰጣሉ:: እነዚህ መሪዎች ከምእመናን ጋር መልካም ግንኙነት ለመመሥረት ተግቶ መሥራት ብቻ ሳይሆን፣ መልካም ግንኙነት ማድረግ እንዳለባቸው ይገነዘባሉ:: በመሆኑም፣ ምእመናንን እንደ ግለሰቦች በማወቅ፣ በአገልግሎታቸው በማበ ረታታት፣ ለቤተሰባዊ ጉዳዮቻቸው ርኅራኄን በማሳየት (ለምሳሌ፣ የቤተሰቡ አባል በሚታመምበት ጊዜ መጠየቅ) ጊዜያቸውን ያሳ ልፋሉ::

መሪዎች ከጊዜያቸው አነስተኛውን የሚያሳልፉት ግን በእነዚህ «አስቸኳይ ባልሆኑና አስፈላጊ ተግባራት» ላይ ነው:: አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት «አስቸኳይና አስፈላጊ» ወይም «አስቸኳይና አስፈላጊ ባልሆኑ» ነገሮች ላይ ነው:: በዚህም ምክንያት፣ መሪዎች ብዙውን ጊዜ አስቸኳይ የሆኑትን ነገሮች በማስተናገድ ላይ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከጊዜያቸው አብዛኛውን የሚያሳልፉት የተጣሉትን አብያተ ክርስቲያናት ወይም መሪዎች ለማስታረቅ በመጣር ነው:: ወይም ደግሞ አስቸኳይ ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ያከናውናሉ:: ነገር ግን መሪዎች የቤተ ክርስቲያናቸውን እድገትና መንፈሳዊ ብስለት የማስደጉን ተግባር እምብዛም አይሠሩም::

33ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውጤታማ መሪ ለመሆን ሊያከናውናቸው የሚገባቸው «አስቸኳይ ያልሆኑ ግን አስፈላጊ ተግባራት» ምን ምንድን ናቸው? ዘርዝራቸው፡፡ ለ) እነዚህ ነገሮች ለአንድ መሪ ለኬት አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው? ሐ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በእነዚህ ነገሮች ላይ ይመስልሃል? ለምን? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእነዚህ ነገሮች ላይ በብቃት ትኩረት አድርገው የማይሠሩ ከሆነ፣ ምን ዓይነት ችግሮች ይከሰታሉ?

**3. አስቸኳይና አስፈላጊ ያልሆኑ ተግባራት፡-** እነዚህ በፍጥነት እንድንደርስላቸው የሚጠይቁ አስቸኳይ ነገሮች ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ግን አስፈላጊዎች አይደሉም፡፡ እንበልና፣ ከአንድ ሰው ጋር ጠቃሚ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እየተነጋገርን ነው፡፡ ይህ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ስልኩ ያቃጭላል፡፡ ስልኩን ስናነሣ፣ የደወለው ግለሰቡ በሚቀጥለው ሳምንት በስንት ሰዓት ስብሰባ እንደሚጀምር ለማወቅ የፈለገ ሰው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስልኩን ከደወለው ሰው ጋር ሰላምታ ስንለዋወጥና ስለ አጠቃላይ ነገሮች ስናወራ አሥር ደቂቃ አባከንን፡፡ ስለ አገልግሎት የምናነጋግ ረው ሰው መሄድ ስላለበት፣ ሥራችንን ለማከናወን ሳንችል ቀረን ማለት ነው፡፡ ስልኩ መነሣት ስለ ነበረበት ጉዳዩ አስቸኳይ ነበር፡፡ ነገር ግን ጸሐፊዋ ምላሽ ልትሰጥ ትችል ስለ ነበረ፣ ጉዳዩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ወይም ደግሞ እኛው ራሳችን በኋላ ደውለን መልሱን ልንነግረው እንችል ነበር፡፡ ወይም ደግሞ የጸሐፊያችን የፎቶ ኮፒ ወረቀት ያልቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ስብሰባውን አቋርጣ በመግባት ገንዘብ እንድትሰጣትና ወረቀቱ እንዲገዛ ትጠይቃለች፡፡ ወይም ደግሞ ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የተወሰነ ቡድን ለምሳ ወጥቶ ብዙ ሰዓት ሊቆይ ይፈልጋል፡፡ በዚህ ኅብረት ላይ በመገኘት ግንኙነታችንን ማጠናከር አለብን የሚል ግምት የለንም፡፡ ነገር ግን ሆቴል ለመብላትና ከሰዎች ጋር ለመነጋገር ስንል አብረናቸው እንሄዳለን፡፡

34ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ነገሮች ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ባይኖርም፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለእርሱ አስቸኳይ መስለው ስለ ታዩት ብቻ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡ ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስቸኳይ ባይሆኑም እንኳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ (እድገት) ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች ላይ ከመሥራት



ይልቅ፣ እንደ እነዚህ ዓይነት ነገሮችን በማድረግ አብዛኛውን ጊዜያቸውን መጠቀም እንዴት እንደሚቀልላቸው አብራራ፡፡

**4. አስቸኳይም አስፈላጊም ያልሆኑ ተግባራት፡-** እነዚህ ነገሮች ጊዜ ከማባከን በቀር ለአመራራችን የሚጨምሩት እሴት የላቸውም፡፡ ለምሳሌ፣ በአሜሪካ አገር ስለሚካሄድ ሰሚናር የሚናገር ደብዳቤ ይላክልንና ለሰብከት ማዘጋጃ ከሚያስፈልገን ጊዜ ላይ ወስደን እናነብበዋለን፡፡ ወይም ደግሞ ሥራችንን ከመሥራት ይልቅ ሻይ እየጠጣን ከጓደኞችን ጋር ስናወራ እንቆያለን፡፡ ወይም ደግሞ አንድን ሰው ለመጎብኘት ሄደን ሠላሳ ደቂቃ ሙሉ ስናወራ እንቆያለን፡፡

35ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አስቸኳይም አስፈላጊም ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውን ጊዜ ሊያባክኑ የሚችሉትን ነገሮች ዘርዝር፡፡ ለ) ጊዜያችንን በአስፈላጊ ነገሮች ላይ እንደ ማከናወን ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ነገሮችን የምናደርገው ለምንድን ነው?

ውጤታማ አመራር ለእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ እድገት የሚያመጡ ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡ እነዚህም «አስቸኳይ ያልሆኑና ዳሩ ግን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች» ናቸው፡፡ እነዚህን አስፈላጊ ነገሮች ለማከናወን፣ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወሱ ጠቃሚ ነው፡፡

- ለማከናወን የምንፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ለማከናወን የሚያስችል ጊዜ በማይኖረን ጊዜ ሁለት ምርጫዎች አሉን፡፡ አንድም አስፈላጊዎቹን ነገሮች ለማከናወን የሚያስችል ጊዜ እናገኝ ዘንድ ሌሎች ተግባራትን መቀነስ፣ ወይም ደግሞ ጊዜያችንን በተ ሻለ መንገድ ለመጠቀም መሞከር አለብን፡፡ ብዙውን ጊዜ ግን የእነዚህን ሁለት ነገሮች ውህደት ልንጠቀም እንችላለን፡፡ አስተዋይ መሪዎች ሁልጊዜም የሚያከናውኗቸውን ነገሮች በመገምገም እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ- «ይህንን ነገር ማድረግ አለብኝ? ወይስ ሌላ ሰው ያድርገው?» ለምሳሌ፣ አስተዋይ መሪ ደብዳቤዎ ቹን ለመጻፍ ራሱ ኮምፒዩተሩ ላይ መተየብ እንዳለበት ወይም ጸሐፊው ይህንን ተግባር ብታከናውን ይሻል እንደ ሆነ ያስባል፡፡

መሪዎች የሚያደርጓቸውን ብዙ ነገሮች ለሌሎች በውክልና ሊሰጡ ይችላሉ። እንዲሁም ደግሞ መሪዎች «አስቸኳይና ዳሩ ግን አስፈላጊ ያልሆኑትን ነገሮች» በማከናወን ብዙ ጊዜ የሚያጠፉ ከሆነ፣ ነገሮች ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ ከመቀየራቸው በፊት ሊያስተካክሉ የሚችሉበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው። ወይም ደግሞ «አስቸኳይም አስፈላጊም» ያልሆኑትን ነገሮች ያደርጉ ይሆናል። እነዚህን ነገሮች በፍጥነት ማቆም አለባቸው።

• መሪው መሠረታዊ ችግሮችን ባለመፍታቱ ምክንያት በአብዛኛው «አስቸኳይና አስፈላጊ» ነገሮችን የሚያከናውን ከሆነ፣ የራሱንና የሌሎችን ሰዎች ጊዜ እያባከነ ነው። ችግሩን የሚያመጡትን መሠረታዊ ችግሮች እንደ መፍታት፣ ከአንዱ ቀውጢ ሁኔታ ወደ ሌላው እየተሸጋገረ ነው ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ መሪ የአረምን ቅጠል ብቻ እንደሚበጥስ ገበሬ ነው። ብዙም ሳይቆይ አረሙ እንደገና ይለመልማል። አረሙ ዳግም እንዳያቆጠቁጥ ከሥሩ ነቅሎ ለመጣል አይሞክርም። መሪው ችግሮቹ ወደፊት እንዳያቆጠቁጡ በሚያስችል መንገድ የችግሩን ምንጮች ማድረቅ አለበት። ይህ «አስቸኳይ ያልሆኑና አስፈላጊ» ተግባራትን የማከናወን ውጤት ነው።

• «አስቸኳይ ያልሆኑትንና ዳሩ ግን አስፈላጊዎቹን» ተግባራት ማከናወን የሚቻለው «አስቸኳይና ዳሩ ግን አስፈላጊ ያልሆኑ» እና «አስቸኳይም አስፈላጊም» ያልሆኑ ነገሮች ላይ የምናጠፋውን ጊዜ በመቀነስ ነው። ተግባሮቻችንን መርምረን ምን ዓይነት መሆናቸውን በማወቅ «አስቸኳይ ባልሆኑና ዳሩ ግን አስፈላጊ» በሆኑ ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን። እምብዛም አስፈላጊ ባልሆኑ ተግባራት ላይ ጊዜያችንን በማጥፋት አስፈላጊ ለሆኑት ነገሮች ጊዜ የማናገኝ ከሆነ፣ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ላለማካሄድ መርጠናል ማለት ነው። በድርጊታችን፣ አስፈላጊ ላልሆኑ ነገሮች «እሺ» የምንል ከሆነ፣ ለአስፈላጊ አገልግሎቶች «እምቢ» ማለታችን ነው።

• ውጤታማነት ማለት ሁሉንም ሚናዎችና ኃላፊነቶች ሚዛናዊ ማድረግ ማለት ነው። የሥራ ጊዜያችንን ከቤተሰብ ጊዜ ያችን፣ የቤተ ክርስቲያን ጊዜያችንን ለማኅበረሰባችን ከምንሰጠው



ጊዜ፣ ወዘተ. . . ጋር ሚዛናዊ እናደርጋለን። በአንድ በኩል ጎበዝ ሆኖ (ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያን አመራር) በሌላው (ለምሳሌ፣ ልጆቻችንን ለዓለማዊነት መዳረግ) መውደቅ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ውጤታማ እንዳንሆን ያደርገናል። ስለሆነም፣ የጊዜ ሠሌዳችንን በምናዘጋጅበት ጊዜ፣ ለሚናዎቻችን ሁሉ ሚዛናዊ ጊዜ ለመስጠት እንድንችል የሕይወታችን ክፍሎች ሁሉ መካተታቸውን ማረጋገጥ አለብን።

• የጊዜ ሠሌዳችን የማይለመጥ (ግትር) በመሆኑ ምክንያት ሰ ዎች እንዳይጎዱ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። በዋናነት፣ ትልቁ ቁም ነገር ሰዎች ናቸው። ምንም እንኳን ሰዎች በአላስፈላጊ ወሬ ጊዜ ያችንን እንዲያባክኑ ባንፈቅድላቸውም፣ በሌላ በኩል የምናገለግለው ለዎችን እንደ ሆነ መዘንጋት የለብንም።

> 36ኛ ጥያቄ:- ሀ) በዚህ ሳምንት ያከናወንካቸውን ነገሮችና እያንዳንዳቸውን ለማከናወን የፈጀብህን ጊዜ ዘርዝር። ለ) ከእያንዳንዱ ድርጊት አጠገብ ከአራቱ ተግባራት የትኛው እንደሚሆን አመልክት። ሐ) ጊዜህን በበለጠ በውጤታማነት ለመጠቀም ብትፈልግ ምን ዓይነት ነገሮችን ትለውጣለህ? «አስቸኳይ ባልሆኑና ዳሩ ግን አስፈላጊ በሆኑ» ተግባራት ላይ የበለጠ ለማተኮር ምን ልታደርግ ትችላለህ?

## አምስተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### *የመወያያ ጥያቄዎች:-*

1. ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ አብዛኞቹ ምእመናን መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን እየተጠቀሙ ነውን? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብዛኞቹ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጸጋ ስጦታዎቻቸውን እንዲጠቀሙ የማያደርጉ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዴት መቀየር አለበት? ሐ) አንተ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ብትሆን፣ ብዙ ምእመናን በጠቃሚ አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ምን እርምጃ ትወስዳለህ?

2. ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማላደግ ሊመሠርት የሚችላቸውን ሦስት ዓይነት ቡድኖች ዘርዝር:: ለ) እያንዳንዱ ዓይነት ቡድን የቤተ ክርስቲያን መሪው አገልግሎቱን በሚገባ እንዲያከናውን የሚያስችልበትን መንገድ ግለጽ:: ሐ) ለቤተ ክርስቲያንህ የወንጌል ስርጭትና የማስተማሪያ ቡድኖችን መሥርት:: በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ እነማንን ታስገባለህ? የእያንዳንዱ ቡድን ሥራ ምን ይሆናል? ከሽማግሌዎችና አገልጋዮች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ምን ዓይነት ይሆናል? መ) ሽማግሌዎች እንደ «ቡድን» ቢሠሩ፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት ይለወጣል? ሠ) ሽማግሌዎችና አገልጋዮች እንዴት በተሻለ ሁኔታ እንደ ቡድን ሊሠሩ ይችላሉ?

3. ሀ) በጎ ፈቃደኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠቃሚ አገልግሎቶችን ሲያካሂዱ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች ብዙ ሰዎች በጠቃሚ አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) በጎ ፈቃደኞች ተስፋ ሳይቆርጡ ተጠናክረው አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ ለማስቻል የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

4. ሀ) በየቀኑ መሪዎችን የሚያጋጥሟቸውን አራት ተግባራት ዘርዝር:: ለ) በየቀኑ አብዛኛውን ጊዜ የሚወስዱት የትኞቹ ተግባራት ናቸው? ሐ) ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥራቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ለማድረግ ምን ዓይነት ዘዴዎችን ይጠቀማል? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስቸኳይ ያልሆኑና አስፈላጊ የሆኑትን» ነገሮች ለማከናወን ይችሉ ዘንድ ጊዜያቸውን እንዴት ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ተወያዩ:: ሠ) አገልጋዮች የጊዜ አጠቃቀማቸውን ባለመቆጣጠራቸውና የመንግሥት ሠራተኞችን ያህል ረዥም ሰዓት አገልግሎታቸው ውስጥ ባለመቆየታቸው ምክንያት እግዚአብሔርን «በሚሰርቁበት» ሁኔታ ላይ ተወያዩ:: ጊዜያቸውን ባለመቆጣጠራቸው እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝባቸው ይመስላችኋል? መልሶቻችሁን አብራርታችሁ ግለጹ::



# ትምህርት አሥራ ሰባት

## አንደኛ ቀን

ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመሆን ከፈለግን፣ ጊዜያችንን ከማባከን ይልቅ ለእግዚአብሔር መንግሥት ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ ነገሮች ላይ ጊዜያችንንና ጉልበታችንን ለማዋል ስንል የጊዜ አጠቃቀማችንን መቆጣጠር አለብን:: እግዚአብሔር የተለያዩ ሰዎችን ይፈጥራል:: አንዳንዶቹ በሚገባ ራሳቸውን ለማደራጀትና የጊዜ ሠሌዳቸውን በቅርብ ለመከታተል ሲፈልጉ፣ ሌሎች ደግሞ በበለጠ እንደ ሁኔታው መቀያየርን ይመርጣሉ:: ይህንንም የሚያደርጉት ጥሩ የጊዜ አጠቃቀም የሚያመጡ ምርጫዎችን የማድረግ ብቃታቸውን በመተማመን ነው:: የግል ዝንባሌያችን ምንም ይሁን ምን፣ ሁላችንም የጊዜ አጠቃቀማችንን ለመመርመር የሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት አለብን:: ይህንንም ስናደርግ ሙሴ ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ጸሎት ማስታወስ አለብን:: ሙሴ እግዚአብሔርን ጥበብን እማር ዘንድ የቀኖቼ ቁጥር ስንት እንደ ሆነ እንዳውቅ አስተምረኝ ነበር ያለው (መዝ. 90:12):: ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጊዜ አጠቃቀማቸውን ለማላደግ ሊያደርጉ የሚገባቸውን የተለያዩ ነገሮች እንመለከታለን::

> 1ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድን ጠቃሚ ነገር ካሰብክ በኋላ ተግባራዊ ከማድረግህ በፊት የረሳህበትን ሁኔታ የሚያስታውስ ምሳሌ ስጥ:: ለ) አንድን አስፈላጊ ነገር ለማስታወስ ምን ታደርጋለህ? ሐ) ሥራ የሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ ሥራዎችን በመዘንጋት ሰዎች እንዲሠሩ ሲጠይቁት ብቻ የሚሠራበትን ሁኔታ አብራራ::

### እግዚአብሔር የሰጠህን ተግባር ለማከናወን እንድትችል የተግባራትን የአስፈላጊነት ቅድመ-ተከተል የያዘ የሥራ ዝርዝር ማዘጋጀት

ነገሮችን ካልጻፍን ልንዘነጋቸው እንችላለን:: ወይም ደግሞ ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮች ጊዜያችንን እንዲያጣብቡ ስለምናደርግ፣ አስፈላጊዎቹን ተግባራት ሳንፈጽም እንቀራለን:: መሪዎች ጊዜያቸውን በብቃት ለመጠቀም ሊገለገሉ የሚችሉት አንደኛ

ው መሣሪያ የረዥምና የአጭር ጊዜ ኃላፊነቶችን ለመወጣትና ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የተግባራት ዝርዝር ማዘጋጀት ነው:: (ማስታወሻ:- ምዕራባውያን ነገሮችን በማከናወን ላይ በማተኮር ሚዛናዊነትን ያዛባሉ:: ብዙ አፍሪካውያን ደግሞ በዝምድና ላይ ያተኩራሉ:: ውጤታማ መሪ መልካም ግንኙነት መጠበቅን ተግባራትን ከማከናወን ጋር ሚዛናዊ ማድረግ አለበት:: ይህንን ሚዛናዊነት ለመወሰን ብዙ ጥረት ይጠይቃል:: የምዕራባውያንን የተግባራት አፈጻጸም በማለየቱ ላይ የሚያተኩረውን ይህንን አሳብ በምታነብበት ጊዜ፣ ግንኙነቶችን ከመጠበቅ ጋር ሚዛናዊ ለማድረግ መጣር እንዳለብህ አትዘንጋ::)

ይህንን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ዝርዝር ለማዘጋጀት የሚያስችሉ አንዳንድ አሳቦች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል::

1. አንድ መሪ በእግዚአብሔር ፊት ውጤታማ ለመሆን ሊያከናውናቸው የሚገቡትን ነገሮች የሚያሳይ ሁሉንም የሕይወት ክፍሎች ያካተተ ዝርዝር እዘጋጅ::

በዚህ ዝርዝር ውስጥ መሪው ለእግዚእብሔር ለማከናወን የሚፈልጋቸው የረዥም ጊዜ ተግባራት ይዘረዘራሉ (ለምሳሌ፣ ለቤተ ክርስቲያን ራእይና ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ሌሎች መሪዎችን ማሠልጠን):: ይህ ዝርዝር በቅርቡ መከናወን ያለባቸውንም ነገሮች ያካትታል:: (ለምሳሌ፣ ለሽማግሌዎች ወርሐዊ ስብሰባ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ለወንጌላውያን ደመወዝ መክፈል):: መሪው ውጤታማ የሚያደርጉትን ነገሮች እያከናወነ መሆኑን ለማወቅ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ይህንን ዝርዝር መመልከት አለበት:: በዚህ ዋና ዝርዝር ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች መካተት አለባቸው:-

ሀ. መሪው ሁሉንም **የኃላፊነት ክልሎች** መዘርዘር አለበት:: (ከታች የቀረበውን ማብራሪያ ተመልከት::) ለምሳሌ፣ 1) እግዚእብሔር፣ 2) ቤተሰብ፣ 3) ሥራ፣ 4) እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ 5) የቀጣና ቤተ ክርስቲያን፣ 6) ማኅበረሰብ፣ እና 7) ራሴ የሚሉትን ሊዘረዝር ይችለል:: መሪው እነዚህን የሕይወቱን ክፍሎች ሚዛናዊ አድርጎ ካልያዘ፣ ውጤታማ ሊሆን ስለማይችል፣



ይህንን ማድረጉ አስፈላጊ ነው:: በቤተ ክርስቲያን አመራሩ ጎበዝ ሆኖ ሳለ፣ ከቤተሰቡ ጋር ጊዜ የማያሳልፍ ከሆነ፣ የኋላ ኋላ አገልግሎቱ መበላሸቱ አይቀርም:: አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት፣ ለመጸለይ፣ ስፖርት ለመሥራት፣ ለማረፍ፣ ወዘተ. . . ጊዜ የማይቀድስ ከሆነ፣ በአገልግሎቱ ውጤታማ ሊሆን አይችልም::

ለ. በእያንዳንዱ የሕይወት ክፍል እግዚአብሔር የሰጠውን ኃላፊነት ለመፈጸም **ሊያከናውናቸው የሚገባቸውን ነገሮች ቅድሚያ በሚሰጥ መንገድ መዘርዝር** አለበት:: ለምሳሌ፣ «ቤተ ሰብ» ከሚለው ሥር ሚስቱና ልጆቹ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ሊጽፍ ይችላል:: የቤተሰብ ሕይወት በጥሩ ሁኔታ እንዲቀጥል ለማድረግ በቤት አካባቢ ማከናወን ያለበትን ሁሉ ሊዘረዝር ይችላል:: ከ«ማኅበረሰብ» ሥር ለቅሶ ቤት መሄድ፣ ለወንጌሉ ክፍት ለሚመስል አንድ ጎረቤቱ መመስከር፣ በማኅበረሰቡ የሥራ ቀን ላይ መገኘት፣ ወዘተ. . . የሚሉትን ሊያሰፍር ይችላል:: ይህ ዝርዝር በዚህ ሳምንትና በዚህ ወር መፈጸም ያለባቸውን እንዲሁም የረዥም ጊዜ ተግባራትን ማካተት አለበት::

ይህን ዝርዝር ማዘጋጀት የሚቻልበት አንደኛው መንገድ ከዚህ በታች ተመልክቷል:: እያንዳንዱ የመሪው የሕይወት ክፍል እንዴት እንደ ተመለከተና ከእያንዳንዱ ክፍል ሥር የሚያከናውናቸው ተግባራት እንደ ተዘረዘሩ ተመልከት:: መሪው ለእግዚአብሔር ውጤታማ የሚሆነው እነዚህን ነገሮች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በማከናወን ነው:: መሪው አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለማከናወን ይችል ዘንድ በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት ነገሮች በአስፈላጊነታቸው ቅድሚያ የተሰጣቸው ናቸው::

የሚሆነው ምን ዓይነት ያልተጠበቀ ሰው ወይም ጉዳይ እንደሚገጥመን ስለማናውቅ ነው:: ይሁንና፣ ይህ አላስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ከማከናወን ይልቅ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች እንድንሠራ የሚመራን ነው:: መሪው ይህንን የጊዜ ሠሌዳ በሚያዘጋጅበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ነገሮች ማሰብ አለበት:-

ሀ. በዛሬው ዕለት መከናወን ያለባቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? እስከ ነገ ሊቆዩ የሚችሉትስ የትኞቹ ናቸው? መሪው በሚከተሉት ሁለት ነገሮች ላይ በመመሥረት ለሥራ ዝርዝሮቹ ቅድሚያ መስጠት አለበት:: በ<u>መጀመሪያ</u>፣ በዝርዝሩ ውስጥ ከጊዜ ጋር የሚቀየር ነገር አለ ወይ? ቃል የገባውን ተግባር ለማከናወን በዚያን ዕለት ምን መደረግ አለበት? ለአንድ ኮሚቴ ማቅረብ ያለበት ሪፖርት ወይም መደወል ያለበት ስልክ አለ? እንዲህ ዓይነቱ ነገር ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል:: <u>ሁለተኛ</u>፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት በዘላቂነት መሥራት ያለበት ነገር ምንድን ነው? ለእነዚህ ነገሮች ቅድሚያ ካልሰጠ፣ አነስተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ነገሮች ጊዜውን በመውሰድ፣ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች እንዳያከናውን ሊያደርጉት ይችላሉ::

ለ. እንዲሁም ደግሞ አንድ መሪ በቀኑ ውስጥ በየትኛው ሰዓት የትኛውን ተግባር በጥሩ ሁኔታ ሊያከናውን እንደሚችል መወሰን አለበት:: ለምሳሌ፣ በየትኛው ሰዓት ነው ስለ ከባባድ ጉዳዮች ለማሰብና ዕቅዶችን ለማውጣት የሚመቸው? ለአንዳንድ ሰዎች እንዲህ ዓይነቶቹን ሥራዎች ማከናወን የሚቻለው ጠዋት ከማንኛውም ሥራ በፊት ነው:: በመሆኑም፣ ጠዋት እንደ ራእይ፣ ዕቅዶች፣ ችግሮችን መፍታት፣ ሥልጠና መስጠት፣ ወዘተ. . . ባሉት ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ:: ከሰዓት በኋላ ደግሞ ለውነታቸው ደከም ሲል እንደ ስልክ መደወል፣ ከባንክ ገንዘብ ማውጣት፣ ደመወዝ መክፈል፣ ከሰዎች ጋር መነጋገር የመሳሰሉትን ተግባራት ያከናውናሉ::

ሐ. ሥራውን ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል? አንዳንድ ነገሮች የሚከናወኑት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ብዙ ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው:: ለምሳሌ፣ ለቤተ ክርስቲያን ራእይ ለማዘጋጀት አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል::



ለቀበሌ ደብዳቤ መጻፍ ግን የ10 ደቂቃ ሥራ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም፣ በአስቸጋሪ ነገሮች ላይ በምንሠራበት ጊዜ፣ በቂ ጊዜ መስጠት አለብን:: ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተከስቶ የቆየውንና መስተካከል ያለበትን የግንኙነት ችግር ለመፍታት ከጠዋቱ 2:30 እስከ 4:00 ሰዓት ያለውን ጊዜ መመደብ ይቻላል:: በ4:30 ተኩል ላይ ከሌላ ሰው ጋር ቀጠሮ እንዳለን ካወቅን፣ በመሐል ያለችውን የሠላሳ ደቂቃ ጊዜ በመጠቀም ፈጠን ብለን ሻይ እንጠጣና ለቀበሌ ደብዳቤ ልንጽፍ እንችላለን::

5. በቀኑ መጨረሻ ላይ፣ የተከናወኑትን ነገሮች ከልስ:: ከዚያም ለቀጣዩ ቀን አዲስ የሥራ ዝርዝር አውጣ:: በአስፈላጊ ነገሮች ላይ በቂ ጊዜ እየሰጠን መሆን አለመሆናችንን በመመልከት የጊዜ አጠቃቀማችንን የምናስተካክለው በዚህ የግምገማ ሂደት ነው:: ይህ ኃላፊነቶቻችንን ሁሉ ለመወጣት የሚያስችለን አሠራር ነው::

6. አነስተኛ የማስታወሻ ደብተር በኪስህ በመያዝ አሳቦች በሚመጡልህ ጊዜ ወዲያውኑ መዝግብ::

ብዙ ጊዜ ከአንድ ሰው ጋር ስትነጋገር አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለህ ትስማማና ወዲያው ትረሳዋለህ:: ወይም ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድክ ሳለህ መሞከር አለብኝ የምትለው አንድ ጠቃሚ አሳብ ይመጣልሃል:: ቤተ ክርስቲያን ደርሰህ ከሰዎች ጋር በምትነጋገርበት ጊዜ ግን፣ ስታስብ የነበረውን ነገር ትረሳዋለህ:: ለዚህ ችግር ብዙ መሪዎች በመፍትሔነት የሚጠቀሙት በኪሳቸው ውስጥ አነስተኛ የማስታወሻ ደብተርና እስክሪብቶ መያዝ ነው:: አንድ ነገር ለማድረግ ሲስማሙ ወይም አንድ ጥሩ አሳብ ሲመጣላቸው ወዲያውኑ ይመዘግቡታል:: ከዚያም ወደ ቢሯቸው ሲደርሱ ወደ ዋናው የተግባራት ዝርዝር ውስጥ ይጨምሩታል::

2ኛ ጥያቄ:- ሀ) ውጤታማ ለመሆን እንድትችል በእያንዳንዱ የሕይወት ክፍል ልታደርጋቸው የሚገቡህን ነገሮች ዘርዝር:: ለ) እግዚአብሔር በሕይወትህ እንድታደርግ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማከናወን እንድትችል በቀጣዩ ሳምንት መፈጸም ያለብህን ነገሮች ዘርዝር:: ከዐበይት ዝርዝሮችህ ውስጥ ምን ምን ነገሮችን እያከናወንክ ነው? ሐ) በሳምንቱ መጨረሻ የተግባራት ዝርዝር ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነገሮችን ለመሥራት እንዴት እንደረዳህ ግለጽ::

ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም «ክህሎት» መሆኑን አስታውስ። በመሆኑም፣ ይህ በተደጋጋሚ ጥረት በማድረግ ልናዳብረው የሚገባን ነገር ነው። በመጀመሪያው አካባቢ፣ በየዕለቱ የምናከናውናቸውን ተግባራት ዝርዝር ማዘጋጀቱ አሰልቺና አላስፈላጊም ሊመስል ይችላል። «መደረግ ያለበትን ነገር አስታውሳለሁ። አስፈላጊ ነገሮችን ለማከናወን እንድችል ጊዜዬን መቆጣጠር እችላለሁ፣» ልንል እንችላለን። ነገር ግን ብዙዎቻችን አስፈላጊ ነገሮችን ዘንግተን አስቸኳይ የሆኑትን ተግባራት በማከናወኑ ሥራ ላይ እንጠመዳለን። ይህ ደግሞ ሳይከናወኑ የቆዩትን ነገሮች ለመፈጸም እንድንጣደፍና ዳሩ ግን ጥራት ያለው ሥራ ሳንሠራ እንዳንቀር ያደርገናል። (ለምሳሌ፣ የስብሰባው ቀን እስኪደርስ ድረስ ሪፖርት ሳናዘጋጅ እንቆያለን። በዚህ ጊዜ በሪፖርቱ ውስጥ መካተት ስላለባቸው ነገሮች በጥልቀት ለማሰብ ስለማንችል፣ የተወሰኑ ነገሮችን ብቻ እንዘረዝራለን።) ነገር ግን ተግባሮቻችንን በአስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል ብንዘረዝርና ለማከናወን ብንጥር፣ ብዙ ሥራዎችን ልናከናውን እንችላለን። በሁሉም የሕይወት ክፍሎች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በምናከናውንበት ጊዜ፣ ይበልጥ ሚዛናዊ የሆነ ሕይወት ይኖረናል። በመጨረሻም፣ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በማከናወን የጊዜ አጠቃቀምን ክህሎት እናዳብራለን። ይህ ደግሞ አንድ ቀን ከክርስቶስ፣ «መልካም አደረግክ፣ በጎና ታማኝ ባሪያ» የሚሉትን ቃላት እንድትሰማ ያስችልሃል (ማቴ. 25:21)።

## በትንሽ ጊዜ ውስጥ እንዴት ብዙ ተግባር ልናከናውን እንደምንችል።

ለማከናወን የምንፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ለማከናወን የሚያስችል ሰፊ ጊዜ አለን ብለን ካሰብን፣ የተግባራት ዝርዝር ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። አብዛኞቹ ውጤታማ መሪዎች ግን ሥራ የሚበዛባቸውና ካላቸው ጊዜ የበዙ ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅባቸው ናቸው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አሳቦች ሥራ የሚበዛባቸው መሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ ለመጠቀም ውጤታማ ሆነው ያገኙአቸው ናቸው፦



1. በተቻለ መጠን ብዙ ነገሮችን ለሌሎች ሰዎች መወከል። ሥራ የሚበዛበት መሪ የግድ ራሱ ማከናወን ያለባቸውን ነገሮች ብቻ መሥራት አለበት። ሌሎች ልክ እንደ እርሱ ወይም ከእርሱ በላይ ሊያከናውኑ የሚችሏቸውን ነገሮች ግን እርሱ ማድረግ የለበትም። መጀመሪያው አካባቢ የውክልና ሂደት ሥራ ለሚበዛበት መሪ ብዙ ጊዜ ሊወስድበት ይችላል። ይህም የሚሆነው የሚወከለው ሰው ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን እንዲችል ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ ሊሆን ስለሚችል ነው። ነገር ግን ግለሰቡ ከሠለጠነ በኋላ መሪውን ስለሚረዳው፣ መሪው በሌሎች ነገሮች ላይ ትኩረት ለማድረግ የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊያገኝ ይችላል።

2. ለማይቻሉ ነገሮች «አይሆንም» የሚል ምላሽ ስጥ። ብዙውን ጊዜ መሪዎች ሰዎችን ለማስደሰት ስለሚፈልጉ፣ በራሳቸው ላይ ሥራ ይከምራሉ። ስለሆነም፣ መሪዎች የግድ ሊፈጽሙ የማይገባቸውን፣ በዘላለም ብርሃን አስፈላጊ ያልሆኑትንና ሌሎች ሰዎች ሊያከናውኑ የሚችሏቸውን ነገሮች ለማከናወን መስማማት የለባቸውም። አስፈላጊ ያልሆነና ጊዜያችንን የሚወስድ ተግባር ለመፈጸም ፈቃደኛ በምንሆንበት ጊዜ፣ በዚያ ጊዜ ተጠቅመን ልንፈጽም የምንችለውን የበለጠ ጠቃሚ ነገር ላለመፈጸም ፈቃደኛ እየሆንን ነው ማለት ነው።

3. በአንድ ጊዜ በአንድ ነገር ላይ ማተኮርን ተማር። ብዙውን ጊዜ መሪዎች ለማከናወን የሚፈልጓቸው ብዙ ነገሮች አሏቸው። ለትንሽ ጊዜ በአንድ ነገር ላይ (ለምሳሌ፣ በሂሳብ ጉዳይ ላይ) እንሠራና ሳንጨርሰው ሌላ ነገር (ለምሳሌ፣ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ደብዳቤ መጻፍ) እንጀምራለን። እንዲህ ስናደርግ ጊዜ እናባክናለን። ምክንያቱም አዲስ ነገር ለማድረግ በምንሞክርበት ጊዜ አሳባችንን መሰብሰብ ስላለብን፣ የጊዜ ብክነት ይከተላል። ስለዚህ ደብዳቤውን ጽፈን ከጨረስን በኋላ በሂሳብ ላይ መሥራቱ ጠቃሚ ይሆናል።

4. ፋይሎችና ለሥራው የሚያስፈልግ መረጃ ሁሉ የት እንዳሉ ለማወቅ በሚያስችል መንገድ በቢሮህ ውስጥ ነገሮችን አደራጅ።

ነገሮች በማይደራጁበት ጊዜ በፍለጋ የምናጠፋው ጊዜ ብዙ ነው:: መልስ መስጠት ያለብንን ደብዳቤ የት እንዳስቀመጥን ሳናውቅ እንቀራለን:: ስለዚህ፣ መደርደሪያውንና ፋይሎችን ስንፈልግ ብዙ ጊዜ እናባክናለን:: ወይም ቦርዱ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የለጠውን ውሳኔ ለማስታወስ እንፈልጋለን:: ቢሮን ማደራጀትና ነገሮችን በተገቢው መንገድ ማስተካከል ጊዜ የሚወስድ ሥራ ነው:: ነገሮች ከተስተካከሉልን በኋላ ግን፣ ብዙ ጊዜ እናድናለን::

5. ሳትረበሽ የምትሠራበትን ቦታ አዘጋጅ:: ብዙ ጸሎትና አሳብ የሚጠይቁትን ነገሮች ለማከናወን ንቁ የምትሆንበትን ሰዓት ምረጥ:: እንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁለት ቢሮዎችን ይጠቀማሉ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ሰው የሚያውቀው ቢሮ አላቸው:: የስልክ ጥሪ የሚቀበሉትና ከሰዎች ጋር የሚገናኙት በዚህ ቢሮ ውስጥ ነው:: ከዚህ ውጭ ሌላም ድብቅ የሥራ ቦታ አላቸው:: ይህንን ቢሮ የሚያውቁት አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው:: ድንገተኛ ጉዳይ ቢያጋጥመው እነዚህ ሰዎች ሄደው ይጠሩታል:: በዚህ ቢሮ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ (ለምሳሌ ከ2-4 ሰዓት) ይሠራሉ:: በዚህ ቢሮ ውስጥ ሆነው ወደ እግዚአብሔር በመጸለይና ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፈቃዱን በመፈለግ ጊዜ ያሳልፋሉ:: ለቤተ ክርስቲያን ራእይ እንደ ማውጣት፣ አንድ ሰው እንድን ጠቃሚ አገልግሎት እንዲያከናውን እንደ ማሠልጠን ወይም ለሚናር እንደ ማዘጋጀት ስላሉት ነገሮች በጥልቀት ያስባሉ:: አንድ ሰው ጠዋት በሁለት ሰዓት ቀጠሮ ለመያዝ በሚጠይቅበት ጊዜ፣ «ሌላ ቀጠሮ አለኝ» ማለት ይችላሉ:: ምክንያቱም ይህ በሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮች ላይ ለመሥራት ቀጠሮ የያዙት ሰዓት ነውና:: ሁሉም ሰው እስከ 4 ሰዓት ድረስ የማይገኙ መሆናቸውን ስለሚያውቅ፣ ጉዳይ ለማስፈጸም የሚመጣው ከዚያ በኋላ ይሆናል:: ድብቅ ቦታ ማግኘት የሚያስቸግር ከሆነ፣ መሪው ጠዋት ማልዶ (ለምሳሌ፣ በ12 ሰዓት) ከቢሮው በመድረስ፣ ባለ ጉዳይ እስኪመጣ ድረስ ማንም ሳይረብሸው ሲሠራ ሊቆይ ይችላል:: ነገር ግን መሪው ሁልጊዜም ሰዎች ከሥራው የሚያደናቅፉት ከሆነ፣ ለሕዝቡ መንፈሳዊ አመራር ለመስጠት የሚያስፈልገውን ጥልቅ አሳብ ለማካሄድ አይችልም::



6. ስልክ የሚቀበል ሰው ማሠልጠን:: በአሁኑ ጊዜ ስልክ ከታላላቅ የጊዜ ቀበኞች አንዱ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሮችን ቀላል ያደርግልናል በሚል ግምት ስልክ ከአጠገባቸው እንዲኖር ይፈልጋሉ:: ወይም ደግሞ ሞባይል ይይዛሉ:: ይህ ማለት ግን አንድ ሰው ስልክ በሚደውልበት ጊዜ (አስፈላጊ ባይሆን እንኳን)፣ ሥራ-ብዙ የሆነው የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚሠራቸውን ነገሮች በመተው ወይም ስብሰባውን በማቋረጥ ለስልኩ ጥሪ መልስ መስጠት አለበት ማለት ነው:: ይህ ደግሞ መሪው ራሱ ሳይሆን፣ ሌሎች ሰዎች ጊዜውን እንዲቆጣጠሩበት ያደርጋል:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ ሥራዎችን በሚያከናውንበት ጊዜ፣ ስልኩን መንቀል (ሞባይልም ከሆነ ማጥፋት ወይም "ሳይለንት" ማድረግ) አለበት:: ስልክ ስብሰባን ይረብሻል:: ይህ ከመሪው ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ አስያዘው ለመጡት ሰዎችም ትሕትና አለማሳየት ነው:: እነርሱ በቀጠሮእቸው ተገኝተው እያናገሩት ሳለ የቤተ ክርስቲያን መሪው ግን በስልክ ጉዳዩን እያከናወነ በቀጠሮአቸው የመጡት ሰዎች ቁጭ ብለው ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ ማድረጉ ትሕትና የጎደለው ተግባር ነው:: ብዙውን ጊዜ ጸሐፊዎች በቂ መረጃ ስለሚኖራቸው፣ ለስልኩ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ:: ወይም ደግሞ ጸሐፊዋ መልእክት ተቀብላ መሪው በኋላ መልሶ እንዲደውል ማድረግ ትችላለች:: ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪው ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀም (እንዲቆጣጠር) እና ባመቸው ሰዓት ላይ በስልክ የተፈለገውን መረጃ ደውሎ ለመስጠት እንዲችል ያስችለዋል:: ወይም ደግሞ ጸሐፊዋ ስልክ የደወለውን ግለሰብ ጥያቄ ሌላ ሰው እንዲመልስ ልታደርግ ትችላለች::

7. ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነገሮችን በተመሳሳይ ሰዓቶች የምታከናውንበትን ልማድ አዳብር:: ግልጽ የሆኑ ድግግሞሽ ተግባራት በሚኖሩን ጊዜ፣ ብዙም ጥረት ሳናባክን በቀላሉ ከአንዱ ወደ ሌላው ልንሸጋገር እንችላለን:: አብዛኞቹ መሪዎች በየቀኑ የሚከተሉት እንድ ዓይነት ቅደም ተከተል ያለው አሠራር መጠቀም ለዚህ ጠቃሚ መሆኑን ይናገራሉ:: ለምሳሌ፣ በየቀኑ ወደ ቢሮአቸው ለመድረስ ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ ከቤታቸው ይነሣሉ:: ድንገተኛ ጉዳዮች ካልገጠሟቸው ሁልጊዜም ጠዋት ከ2-4 ሰዓት

በጸጥታ ይሠራሉ:: በዚህ ጊዜ እንደ ዕቅዶችና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጣቸውን ግቦች እንዴት እንደሚያሳኩ በጥልቀት ያስባሉ:: ከ4-5 ሰዓት ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ጋር በመገናኘት ሥራቸውን ሊከልሱና ሥልጠና በመስጠት ሊያሳልፉ ይችላሉ:: ከ5-6 ሰዓት ከሌሎች ሰዎች ጋር ስብሰባ ሊኖራቸውና የስልክ ጥሪዎችን ሊመልሱ ይችላሉ:: በ7 ሰዓት ወደ ባንክ ቤት ሊሄዱ፣ ወዘተ. . . ይችላሉ:: በዚህ ዓይነት በመደበኛነት የሚከተሉት የጊዜ ሠሌዳ በሚኖርበት ወቅት፣ አእምሯቸውን ብዙም ሳያስጨንቁና ጊዜያቸውን ሳያባክኑ ሥራዎቻቸውን ማከናወን ይችላሉ::

8. <u>ትናንሽ ነገሮችን ጊዜ ሳትሰጥ ወዲያውኑ አከናውን</u>:: መሪዎች ብዙውን ጊዜ ሥራዎችን ለኋላ በማቆየት የጊዜ ብክነት ይጋብዛሉ:: እንበልና አንድ መሪ በስብሰባ ላይ እንዲገኝ የሚጠይቅ ደብዳቤ ይደርሰዋል:: ነገ መልስ እሰጣለሁ በማለት ደብዳቤውን ፋይል ውስጥ ይከተዋል:: ከሁለት ሳምንታት በኋላ ደብዳቤውን ያገኝና ምላሽ ለመስጠት ይወስናል:: አሁን መልስ ከመስጠቱ በፊት ደብዳቤውን እንደገና ማንበብ ሊኖርበት ነው:: ወይም ደግሞ ጸሐፊው ደብዳቤውን እንድትጽፍለት ሊጠይቅ ይችላል:: ይህ ደግሞ ደብዳቤውን ለሁለተኛና ለሦስተኛ ጊዜ ከማንበብ ያድነዋል:: ወይም ደግሞ ከአንድ ወንጌላዊ የገንዘብ ጥያቄ ይቀርብለታል:: መሪው ገንዘቡ እንዳለ ያውቃል:: በዚህ ጊዜ ሌላ ቀጠሮ ከመስጠት ይልቅ፣ ወንጌላዊው ደመወዙን እንዲቀበል የሚያስችል ወረቀት ጽፎ ቢሰጠው ጊዜውን ለማዳን ይረዳዋል:: መሪው ወደ ትናንሽ ጉዳዮች ደጋግሞ በሚመለስበት ጊዜ፣ እንደገና ስለ ጉዳዮቹ በማሰብ ጊዜውን ያባክናል:: ስለዚህ መጀመሪያውኑ ለነገሮች መፍትሔ መስጠቱ ጠቃሚ ነው::

> 3ኛ ጥያቄ:- እነዚህን ስምንት አሳቦች ከልስ:: እነዚህ አሳቦች ሥራ የሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን እንዴት እንደሚረዱት ግለጽ::

9. ውጤታማ <u>የስብሰባ አሠራር ተከተል</u>:: የቤተ ክርስቲያን መሪ አብዛኛው ጊዜ የሚጠፋው በስብሰባዎች መሆኑ ይታወቃል::



ብቃት የሚጎድላቸው ስብሰባዎች የመሪውን አብዛኛውን ጊዜ ያባክናሉ:: ስብሰባዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት ወሳኝ መሣሪያዎች ወይም የጊዜ ማባከኛ ሊሆኑ ይችላሉ:: መሪው ስብሰባዎችን የሚያዘጋጅበትና የሚቆጣጠርበት መንገድ መንግሥቱን ለማስፋት ወይም ጊዜ ለማባከን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ይወስናል:: ከዚህ በታች የቀረበው አሳብ መሪዎች ለሚሳተፉባቸው የተለያዩ ዓይነት ስብሰባዎች እገዛ የሚያደርግ ነው:-

ሀ. ከግለሰቦች ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች:- ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከግለሰቦች ጋር ይሰባሰባሉ:: ለእነዚህ ስብሰባዎች መሪው የጊዜ ገደብ ካላበጀ፣ ብዙ ጊዜ ሊባክን ይችላል:: ለሚያናግሯቸው ሰዎች አንድ ሰዓት ብቻ ነው ያለኝ ካላሏቸው፣ ስብሰባው ሁለትና ሦስት ሰዓት ሊወስድ ይችላል:: ነገር ግን ከአንድ ሰዓት በኋላ ሌላ ቀጠሮ አለኝ ካሉ፣ ጉዳዩ በተባለው ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ ይችላል:: ከሰዎች ጋር በምንሰባሰብበት ጊዜ ቶሎ ብለን ልንሸኛቸው እንደ ፈለግን ሳይሆን፣ እንደምናስብላቸው መረዳታቸው ወሳኝ ነው:: ሰዎች የልባቸውን አሳብ የሚገልጹት ዘና አድርገን ስናነጋግራቸው ነው:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ስለ ቤተሰባቸውና ስለ ሕይወታቸው ስንጠይቃቸው ነው:: እንዲሁም ደግሞ ከጸሐፊያችንና ከሌላ ሰው ጋር ባለመነጋገርና ስልክ ባለመጠቀም ለእነርሱ ያለንን አሳቢነት ልናሳይ እንችላለን:: በጠረጴዛችን ላይ ያሉትን ወረቀቶች ከማገላበጥ ይልቅ ፊት ለፊት እንመለከታቸዋለን:: ሰዎች ከልባችን እያዳመጥናቸው መሆናችንን በሚያምኑበት ጊዜ፣ ከእኛ ጋር ያሳለፉት ጊዜ እርኪ ሆኖ ያገኙታል:: ነገር ግን እንዳጣደፍናቸው ወይም ለእነርሱ ግድ እንደሌለን በሚያስቡበት ጊዜ፣ በንዴት ስሜት ይለናበታሉ - ምንም እንደማናስብላቸው እያሰቡ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግሮችን በመግለጽና በችግሮች ላይ በመወያየት በገርነት ሰዎችን መምራት አለባቸው:: በትምህርት 14 ውስጥ የተመለከትነው ሁኔታውን ለመረዳት በሚያስችል መንገድ የማዳመጥ ክህሎት መሪው ከግለሰቦች ጋር በሚሰባሰብበት ጊዜ ጠቃሚ ውጤት እንዲያስመዘግብ እገዛ ያደርግለታል::

ለ. ኮሚቴዎች:- ሰሎሞን ብዙ አማካሪዎች መኖራቸው ብዙ ጥበብ እንዲኖረን እንደሚያደርግ ተናግሯል (ምሳሌ 15:22)። ዛሬ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ አማካሪዎች ብዙውን ጊዜ ኮሚቴዎች ናቸው። ነገር ግን መሪው ካልተጠነቀቀ፣ እነዚህ ኮሚቴዎች ብዙ ጊዜ ሊያባክኑበት ይችላሉ፡ ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ኮሚቴ የሚከተሉትን ምክሮች ይሰጣሉ:-

1) የቤተ ክርስቲያን መሪ በተቻለ መጠን ጥቂት የኮሚቴ ስብሰባዎችን መካፈል አለበት። ነገር ግን፣ ሌሎችን ሰዎች በመወከል (ትምህርት 11) ለኮሚቴዎች መመሪያዎችን ሊሰጥና በዚህ ዓይነት ሥራዎች ላይ ልምድ ያለውን ሰው በሊቀ መንበርነት በመሾም (ለምሳሌ፣ በሰንበት ትምህርት ቤት ሥልጠና የወሰደ ሰው የዚሁ ኮሚቴ ሊቀ መንበር እንዲሆን በማድረግ) ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ሊያግዛቸው ይገባል። ዝርዝር ውሳኔዎች በአገልግሎቱ ውስጥ ባሉት ሰዎች ቢሰጡ መልካም ነው። ስለ-ሆነም፣ ወንጌላውያንና ረዳቶቻቸው የወንጌል ስርጭት ዕቅዶችንና ውሳኔዎችን አዘጋጅተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ችግረኞች ለመርዳት ደግሞ ዲያቆናት ወይም የልማት ሠራተኞች ዕቅዶችን ቢያወጡ የተሻለ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በአገልግሎቱ ውስጥ ተሳታፊ ባልሆኑ መሪዎች መከናወን የለበትም።

2) የቤተ ክርስቲያን መሪው የኮሚቴ አባላትን በጥንቃቄ መምረጥ አለበት። የኮሚቴው ውጤታማነት የሚለካው በአባላቱ ችሎታ ነው። አባላቱ በጥበብ ከተመረጡ፣ ኮሚቴ ከመሪው የበለጠ ጠቃሚ ውሳኔዎችን ሊሰጥ ይችላል። ሥራውን ተግባራዊ የሚያደርጉት ራሳቸው ስለሆኑ፣ ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት ይፈልጋሉ። እንዲሁም ደግሞ ከሽማሌዎች በላይ ቀጥታ የአገልግሎቱ ተሳታፊዎች በመሆናቸው፣ ብዙውን ጊዜ ምን ከሁሉም የተሻለ ውጤት እንደሚያመጣና ምንስ ደካማ ውጤት እንደሚያስከትል ያውቃሉ። ከቤተ ክርስቲያን መሪው የበለጠ ስለ ሥራው ከማወቃቸውም በላይ፣ በጉዳዮቹ ላይ በጥልቀት ለማሰብ ከቤተ ክርስቲያን መሪው የተሻለ ጊዜ አላቸው።



3) መሪው ኮሚቴው የሚመራበትን ግልጽ መመሪያ ማዘጋጀት አለበት። ኮሚቴዎች ተጠያቂነታቸው ለማን እንደ ሆነ፣ ምን ዓይነት ውሳኔዎችን መስጠትና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ፣ ወዘተ. . . ማወቅ አለባቸው። እነዚህ መመሪያዎች ካልታወቁ፣ ብዙውን ጊዜ በኮሚቴውና በሽማግሌዎች መካከል አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። የቤተ ክርስቲያን መሪው ኮሚቴው የፈጠራ ችሎታ ያለው እንዲሆንና ነገሮች ባቀዱት መንገድ ባይከናወኑ መጨነቅ እንደሌለባቸው ማስታወቅ አለበት። ከስሕተታቸው እስከ ተማሩና በሚቀጥለው ጊዜ የተሻለ ሥራ ለመሥራት እስከ ቻሉ ድረስ፣ ይህ ችግር ሊሆን አይገባም። ሰዎች እሳሳታለሁ በሚል ፍርሃት ከተሸበቡ፣ ምን ጊዜም ጥሩ ውሳኔዎችን ሊሰጡ አይችሉም። መሪዎች የሚተገብሯቸውን ጊዜያዊ አሳቦች ብቻ ያቀርባሉ። ይህ ደግሞ መሪው ሌሎች ነገሮችን ለማከናወን የሚችልበትን ጊዜ እንዲያገኝ አይረዳውም።

4) እያንዳንዱ ኮሚቴ ስለ አገልግሎቱ ኃላፊነትና ሥልጣን ሊሰጠው ይገባል። የቤተ ክርስቲያን ቦርድ የኮሚቴዎችን የውሳኔ ሰጭነት ኃይልንና ዕቅዳቸውን እንደሚያጸድቅ ይወስናል። ነገር ግን በተሰጣቸው ሥልጣን ክልል ኮሚቴዎች እግዚአብሔር የሚናገራቸውን ነገር የማከናወን ነጻነት ሊኖራቸው ይገባል። ሰዎች በኮሚቴ ውስጥ ዕቅዶችን አውጥተው ተግባራዊ እርምጃዎችን ማከናወን በሚችሉበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር በሚያከናውኑት ሥራ ደስተኞች ይሆናሉ። ነገር ግን፣ ውሳኔ መስጠት የማይችሉ ከሆነ፣ ኮሚቴዎች ሙሉ ትኩረት ሊሰጣቸው የማይገባቸው መሆናቸውን በማሰብ በተቻላቸው መጠን አነስተኛ ተግባር ብቻ ያከናውናሉ። ይህ መሪውን አይረዳውም።

5) የቤተ ክርስቲያን መሪው የሁሉንም አገልጋዮች ቃለ ጉባኤ መቀበል አለበት። ይህ እያንዳንዱ ኮሚቴና የአገልግሎት ዘርፍ ምን እያከናወነ እንዳለ እንዲገነዘብ ያስችለዋል። ከኮሚቴው ውሳኔዎች አጥጋቢ ሆኖ ያላገኘው ካለ፣ ውሳኔውን ለመጫን መሞከር የለበትም። ይህንን ማድረጉ የኮሚቴውን ተነሣሽነት በመቀነስ ኃላፊነቱንና ሥልጣኑን ወደ የቤተ ክርስቲያን መሪው

ሊመልስ ይችላል:: ይህ ደግሞ መሪው ውሳኔዎችን ሁሉ ለመስጠት እንዲገደድ ያደርገዋል:: የሥራ ጫናው እንደገና ይጨምራል:: የሚጠራጠረው ውሳኔ ካለ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ከኮሚቴው ሊቀ መንበር ጋር መነጋገር አለበት:: ውሳኔውን ለምን እንደ ሰጡ ካወቀ በኋላ፣ በጉዳዩ ላይ የራሱን አመለካከት ማቅረብ አለበት:: ከዚያ በኋላ የኮሚቴው ሊቀ መንበር ወደ ኮሚቴው በመመለስ የበፊት ውሳኔያቸው ምርጥ ሳይሆን የሚችልባቸውን ምክንያቶች ማስረዳት አለበት:: ከዚያ በኋላ የኮሚቴው አባላት የራሳቸውን ውሳኔ መስጠት አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪው ካሳመናቸው፣ እሳባቸውን ይቀይራሉ:: ካሳሳመናቸው ግን፣ የራሳቸውን ውሳኔ የመስጠትና ካልሠራም ከስሕተታቸው የመማር ነጻነት ሊሰጣቸው ይገባል::

6) የቤተ ክርስቲያን መሪው የኮሚቴውን ሊቀ መንበር ውጤታማነት በማሳደግ የኮሚቴውን ብቃት ማሳደግ እለበት:: ስለ-ሆነም መሪው ከኮሚቴው ሊቀ መንበር ጋር ስለ ቤተ ክርስቲያን እገልግሎቶች መወያየትና ያሳያቸው ነገሮች ካሉ ልብ እንዲሳቸው ማስታወስ ይኖርበታል:: (ለምሳሌ፣ አዲስ የድምጽ ሲስተም መግዛት የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት እንዴት ሊቀይር ይችላል? ሁልጊዜም በዚህ መንገድ የምናመልክ ከሆነ፣ በተለየ መንገድ ማምለክ የሚፈልጉ ሰዎች ምን ዓይነት ስሜት ይሰማቸዋል? ለእገሌ የገንዘብ ስጦታ ሰጥተሃል:: እብራው የምትሠራው እኅት ይህንን ስታውቅና ለእርሷ ግን ምንም ስጦታ እንዳልተሰጣት ስትገነዘብ ምን ይሰማታል?)

ሐ. የሽማግሌዎች ወይም የቦርድ ስብሰባዎች፡- እንድ መሪ ለሌሎች የማይወክሰው እንደኛው ዓይነት ስብሰባ ብዙውን ጊዜ በወር አንድ ጊዜ የሚካሄደው የሽማግሌዎች ስብሰባ ነው:: በተለይ ይህ ስብሰባ በተደጋጋሚ የሚካሄድ በመሆኑ፣ ሽማግሌዎችና የቤተ ክርስቲያን እገልጋዮች እየተዳከሙ ሊሄዱ ይችላሉ:: እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተለያዩ የቦርድ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ኃላፊነት እለባቸው:: የቦርድ ስብሰባውን ውጤታማ ማድረግ የመሪው ኃላፊነት ነው:: በእነዚህ ስብሰባዎች



ላይ የሚገኙት በጣም ሥራ የሚበዛባቸው ሰዎች ናቸው:: የቦርድ አባላት ክሩቅ ቦታዎች መጥተው ስብሰባውን እንዲካፈሉ ለማስቻል ብዙ ገንዘብም ሊወጣ ይችላል:: በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ እጅግ ጠቃሚ የቤተ ክርስቲያን ውሳኔዎች ስለሚሰጡ፣ በዚህ መሐል የሚባክን ማንኛውም ጊዜ ጥሩ ውሳኔዎች እንዳይሰጡ የበኩላቸውን አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ:: እነዚህ ስብሰባዎች ውጤታማ እንዲሆኑና የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች በበቂ ሁኔታ እንዲዳሰሱ ለማስቻል፣ የቦርድ ስብሰባዎችን የመምራት ኃላፊነት ያለባቸው ሰ ዎች ክፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል:: (ማስታወሻ፡- የቤተ ክርስቲያን መሪው የሽማግሌዎችንና የቦርድ ስብሰባዎችን ውጤ ታማ ለማድረግ ምን ማድረግ እንዳለበት ለመረዳት የትምህርት 13ን፣ አንደኛ ቀን ትምህርት ክልስ::)

4ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተመለከቱትን አሳቦች በመጠቀም፣ ሀ) ከቤተ ክርስቲያን መሪ ጋር የምታካሂደው ስብሰባ እንዴት ውጤታማና ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ግለጽ:: ለ) የተሳተፍክበት የኮሚቴ ወይም የቦርድ ስብሰባ ይበልጥ ብቃት ባለውና የመሪውን ጊዜ በሚቆጥብ መንገድ ሊካሄድ ይችል የነበረበትን መንገድ ግለጽ::

## ሁለተኛ ቀን

ሌሊት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዶሃል እንበል:: አንድ ሌባ ቀስ ብሎ መስኮቱን በመክፈት ወደ ቤትህ ገብቶ ገንዘብህንና ቴፕህን ወሰደብህ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ምንም ኮሽታ እልሰማህም ነበር:: ነገር ግን ጠዋት ስትነሣ፣ ለብዙ ወራት ገንዘብ አጠራቅመህ የገዛኸው ቴፕ ተሰርቋል:: ይህ ምን ያህል እንደሚያሳዝን እስበው:: ነገር ግን በየቀኑ ውድ ንብረትህን የሚሰርቅ ሌላ ዓይነት ሌባ እለ:: ይህም ሌ ባ ጊዜህን የሚያባክን ነገር ነው:: እኔና እንተ የምንኖርባት እያንዳንዷ ደቂቃ እግዚአብሔር እንድናገለግለው የሰጠን ውድ ስጦታ ናት:: ነገር ግን ከዚህ ጊዜ ውስጥ ሳናውቅ የሚወሰድብን ምን ያህሉ ነው? ምን ያህል ጊዜ እንደ ተዘረፍን የምናውቀው ከሞት ጋር በምንጋፈጥበት ጊዜ ሕይወታችንን መለስ ብለን ስንመለከት ብቻ ነው:: በቀን የእንድ ሰዓት ሥራ ብናባክን፣ በዓመት የአንድ ወር ያህል ጊዜ እናባክናለን፡ የቤተ ክርስቲያን

ሠራተኞች ከሆንን፣ ክቤተ ክርስቲያን የአንድ ወር ደመወዝ ሰርቀናል ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ህብት ታማኝ ባለ አደራዎች ለመሆን ከፈለግን፣ ጊዜያችንን በመስረቅ እግዚአብሔርን የሚያስክብር አገልግሎት ለመስጠት እንዳንችል የሚያደርጉትን ነገሮች ለይተን ማወቅ አለብን::

## የጊዜ ቀበኞች

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ:- በሕይወትህ ጊዜህን የሚያባክኑትን ነገሮች ዘርዝር:: |

ዛሬ ጊዜያችንን በመስረቅ የሚገባንን ያህል ውጤታማ እንዳንሆን የሚያደርጉትን ነገሮች እንመለከታለን::

1. አንድን ነገር ሳይፈጽሙ መዘግየት:-

ሁለት የመዘግየት ዓይነቶች አሉ:: <u>በመጀመሪያ</u>፣ አንድ ሥራ ወዲያውኑ የማይጀመርበት ሁኔታ ይኖራል:: ለምሳሌ፣ በሁለት ሰዓት ቢሮ መድረስ እያለብን፣ በጊዜ ከቤታችን ካልተነሣን፣ ዘግይተናል ማለት ነው:: ዜና በማዳመጥ፣ ከልጆቻችን ጋር በመጫወት፣ ጋዜጣ በማንበብ፣ ወዘተ. . . ልናረፍድ እንችላለን:: ይህ ደግሞ አሥራ አምስት ደቂቃ አርፍደን ከቢሮአችን እንድንደርስ ያደርገናል:: አሥራ አምስት ደቂቃ አባክነናል ማለት ነው:: ወይም ደግሞ በሰዓቱ ከቢሮአችን እንደርስና ለሥራ ስላልተዘጋጀን፣ ለሰ ዎች ሰላምታ በመስጠት፣ በጠረጴዛችን ላይ ወረቀቶችን በማስተካከል፣ ወዘተ. . . እንቆያለን:: በውስጣችን ሥራ ለመጀመር የማይፈልግ የሆነ ነገር ስላለ፣ በጊዜ ከሥራ ቦታችን አንገኝም:: እዚያ ስንደርስ ደግሞ በፍጥነት ሥራችንን አንጀምርም:: ብዙውን ጊዜ አንድን ጠቃሚ ሥራ የምንጀምረው ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ነው:: ይህ ደግሞ 1 ሰዓት እንድናባክን ያደርገናል::

<u>ሁለተኛው</u> ዓይነት መዘግየት ደግሞ አስፈላጊና ዳሩ ግን አስቸጋሪ የሆኑትን ነገሮች ሳናከናውን ስንቆይ የሚፈጸም ነው:: እነዚህን አስፈላጊ ኃላፊነቶች «እሺ ነገ» እያልን ሳንፈጽም እንቆያለን:: ለቤተ ክርስቲያናችን ራእይ ለማዘጋጀት ማሰብ እንዳለብን እያወቅን፣ ሌላ «ይበልጥ አመቺ» የሆነ ጊዜ እንዲመጣ



እንጠብቃለን:: ወይም ደግሞ በወሩ መጨረሻ ላይ ለመሪዎች ሪ ፖርት ማቅረብ እንዳለብን እያወቅን፣ የስብሰባው ጊዜ እስኪደርስ ድ ረስ ሳናዘጋጀው እንቆያለን:: አሁን ጥናት ለማድረግ የሚያስችል ጊዜ ስለሌለን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያስደስት ነገር ብቻ ለማቅረብ እንሞክራለን:: ይሁን እንጂ፣ ጥሩ ሥራ እንዳልሠራን ልባችን ያውቀዋል:: ወይም ደግሞ አንድ ለማስተካከል የሚቸግረን ነገር እናይና የሆነ ቀን ችግሩ በራሱ መንገድ ይወገዳል ብለን እንጠብቃለን:: ለምሳሌ፣ አንድ መሪ በወሲብ ኃጢአት መውደቁን እንሰማለን:: ሰውዬውን መጋፈጥ ስለማንፈልግ፣ ዝም ብሰን እየጸለይን ከኃጢአቱ እንደሚናዘዝ ተስፋ እናደርጋለን:: ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ኃጢአቱ የመሪውን ቤተሰብ፣ ሌሎች መሪዎችንና በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያንን መጉዳት ይጀምራል::

ለለዚህ መዘግየት የመሪዎችን ጊዜ ከሚያባክኑ ታላላቅ ጠላቶች አንዱ ነው:: በእመዛኙ መሪዎች የመዘግየትን ችግር አይመለከቱም:: አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች እያከናወንን ያለመሆኑን እውነታ በመደበቅ፣ በሌሎች ሥራዎች ላይ ጠደፍ ጠደፍ እንላለን:: የኋላ ኋላ መዘግየቱ ይታወቃል::

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ:- በሕይወትህ እነዚህ ሁለት ዓይነት የመዘግየት ሁኔታዎች እንዴት እንዳጋጠሙህ ግለጽ:: |

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሮችን ሳይፈጽሙ የሚዘገዩባቸው መንገዶችና ውጤቶቻቸው:-

1) ኃጢአት የሚሠሩትን ወይም የተሳሳተ ነገር የሚያደርጉትን ሰዎች እንጋፈጥም:: የሰዎችን ኃጢአት መጋፈጥ የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን መሪ የለም:: ሐሜትን እየዘራች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል የምትፈጥር አባል አለች እንበል:: ባህሉን በሚጠብቅ መንገድ ይህችን እኅት በመጋፈጥ ይህ ጥሩ ሥራ እንዳልሆነ መናገር እንዳለብን እናውቃለን:: ነገር ግን መጋፈጡ አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ አመቺ ጊዜ እንዲመጣ እንጠብቃለን:: ነገር ግን የሐሜቱ «መርዝ» በመስፋፋቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ቤተሰቦች ጸብ ውስጥ ይገባሉ:: ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪው ሰላምን ለማምጣት ሐሜት የምትዘራውን

ሌት ከማጋፌጥ የበለጠ ከባድ ሥራ ለማከናወን እንዲገደድ ያደርገዋል። መጀመሪያውኑ ሐሜቱን መቆጣጠሩ ምንኛ ይቀል ነበር!

2) ሥራውን በሰዓቱ አለመጨረስ። አንድ ሽማግሌ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ በወንጌል ለመድረስ የሚቻልበትን መንገድ አጥንቶ ሪፖርት ለማቅረብ ተስማምቷል። ነገር ግን ለስብሰባው የሚያቀርበውን ጥናት አላዘጋጀም። ስውዬውን ለማጋፌጥ ስለማትፈልግ፣ ሪፖርቱ ለሌላ ወር ይተላለፋል። ሥራው ሳይካሄድ ይቀራል። ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለማቅረብ ቃል መግባቱን በማስታወስ ልትጋፈጠው እንደሚገባ ታውቃለህ። ነገር ግን ከወር ወር ሳትጋፈጠው ትቆያለህ። በመጨረሻም ራስህ ሪፖርቱን አዘጋጅተህ ታቀርባለህ። ይህን ችግር ለማስወገድ ጥረት አለማድረግህ የሚከተሉትን ነገሮች ያስከትላል፦ ሀ) ሽማግሌው ቃሉን መጠበቅ እንዳለበት በማወቅ በመንፈሳዊ ሕይወቱ አያድግም። አደርጋለሁ ያለውን ነገር ካላደረገ፣ ተጠያቂ እንደማይሆንና ሌላ ሰው ሥራውን እንደሚያከናውን አስተምረኸዋል። ለ) ማንም ሰው ወደፊት አንድን አስፈላጊ ነገር ያደርጋል ብሎ እምነት አይጥልበትም። ከእንግዲህ የሚታመኑበት መሪ አይሆንም። ሐ) ለሌላ አገልግሎት ልንጠቀምበት የምንችለውን ጊዜ አጥተናል። መ) ለጎረቤቶቻችን ውጤታማ ምስክርነት ልንሰጥ የምንችልባቸውን ብዙ ወራት ያለ ምንም ሥራ አባክነናል። ከዚህ የተነሣ ወንጌልን ሳይሰሙ ሞተው ወደ ሲኦል የወረዱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደ ቤተ ክርስቲያን፣ «ደማቸው» በእኛ ላይ ነው (የሐዋ. 20:26-27)።

3) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአምልኮ ላይ የበለጠ ኃላፊነት ሊሰጠው የሚገባ ስጦታ ያለው ሰው እንዳለ እናውቃለን። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ሳንነጋገርና ሥልጠና ሳንሰጠው እንቆያለን። ይህ ደግሞ ግለሰቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግልበትን ዕድል ያራዝምበታል። በመጨረሻም ትዕግሥት በማጣቱ ምክንያት ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይሄድና እግዚአብሔር በታላቅ ኃይሉ ይጠቀምበታል። ብዙውን ጊዜ ስጦታ ያላቸው ሰዎች በመሪዎች ላይ ትዕግሥት ያጣሉ። ይህም የሚሆነው መሪዎች ብቃት ስለሚጎድላቸውና ነገሮችን በቀጠሮ እያሳለፉ በርካታ ተግባራት ሳያከናውኑ ስለሚቀሩ ነው። በመሆኑም፣ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ዕድሉን ወደሚያገኙባቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይሄዳሉ። ወይም ደግሞ ሽማግሌዎች በቦርድ ስብሰባቸው ላይ ለአስቸጋሪ ውሳኔዎች ውሳኔ መስጠትን ያዘገያሉ። ውሳኔውን የሚጠብቁ ሰዎች ደግሞ በሽማግሌዎቹ ይናደዱና አያከብሯቸውም።

4) እንደ መሪዎች ችግሮችን መፍታት ብቻ ሳይሆን፣ ለቤተ ክርስቲያን ራእይ መንደፍ እንዳለብንም ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ራእዩን እንዲያሳየን በጸሎት መጠየቅ አለብን። ነገር ግን ይህንን አስፈላጊና ዳሩ ግን አጣዳፊ ያልሆነ ተግባር ሳናከናውን እንዘገያለን። ከዚህ ይልቅ፣ ለመሥራት ደስ የሚሉንን ሥራዎች ማከናወናችንን እንቀጥላለን። ስለዚህ ደብዳቤዎችን በመጻፍ፣ ደመወዝ በመክፈል፣ ሰዎችን ከቢሮ ቢሮ እየዞርን በማነጋገር፣ ወዘተ. . . ጊዜያችንን እናጠፋለን። ለቤተ ክርስቲያን ራእይና ምሪት የመስጠቱን ተግባር ከቶውንም አናከናውንም። ነገሮች ሁልጊዜም የምንሰጣቸውን ጊዜ ተስፋፍተው ሊሞሉ ይችላሉ። ስለሆነም አስፈላጊና ዳሩ ግን አጣዳፊ ያልሆኑትን ተግባራት ለማከናወን የበለጠ አመቺ ጊዜ የምንጠብቅ ከሆነ፣ ይህ ጊዜ መቼም አይመጣልንም። አንድ መሪ እንደተናገረው፣ ውጤታማ መሪዎች ጊዜ በሚወስዱባቸው 80 በመቶ ሥራዎች ላይ ሳይሆን ቅድሚያ በሚሰጧቸው 20 በመቶ ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ነገር ግን ውጤታማ ያልሆኑ መሪዎች አምብዛም አስፈላጊ ባልሆኑ 80 በመቶ ሥራዎች ላይ በማተኮርና ሊያከናውኗቸው የሚገባቸውን ወሳኝ ጉዳዮች ቸል በማለት ሥራዎችን ያዘገያሉ።

5) በቤተ ክርስቲያናችን እንዴት ውጤታማ የወጣቶች ፕሮግራም ማዘጋጀት እንደምንችል የሚያስረዳ ሴሚናር ተካፍለናል እንበል። በሴሚናሩ ላይ ባገኘነው አዲስ አሳብ በጣም ስለ ተደሰትን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ስንመለስ የወጣቶችን ፕሮግራም በማዘጋጀቱ ሥራ ላይ እንጠመዳለን። ከሁለት ቀናት በኋላ ግን፣ ሌ

ሎች አገልግሎቶች ያዘናጉንና ሥራውን ለማከናወን የነበረንን ጉጉት እናጣለን:: በየሳምንቱ የወጣቶቹን ፕሮግራም ማዘጋጀት እንዳለብን ብናውቅም፣ ሌሎች ነገሮች ጣልቃ ይገቡብናል:: ይህ ደግሞ የወጣቶች ፕሮግራም በአሳብ ደረጃ እንዲቀር ያደርገዋል:: ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታየው ችግር አንድ ሥራ እንዴት እንደሚሠራ አለማወቅ አይደለም:: ትልቁ ችግር ነገሮችን ሳያከናውኑ ማዘግየት ነው:: መሪዎች አንድን ሥራ ከጀመሩ በኋላ ለመቀጠል የሚያስችል ፍላጎት በሚያጡበት ጊዜ፣ የመጀመሪያውን የሥራ ጉጉት መልሶ ማምጣቱ አስቸጋሪ ይሆናል:: ሥራውን እስክንጨርስ ድረስ በተጋጋለ ስሜት መቀጠሉ ቀላል ነው:: የምንጀምራቸውን አስፈላጊ ሥራዎች በማንጨርስበት ጊዜ፣ ሰዎች እንደ ሰነፍ መሪዎች ይቆጥሩናል:: አመራራችንን ለማሳየት እጅግ ውጤታማ ከሆኑት ነገሮች አንዱ አንድን ሥራ መጀመርና እስከ ፍጻሜው ድረስ መሥራት መቻል ነው:: ሰዎች አርኪ የተግባር ክንውኖችን በሚመለከቱበት ጊዜ፣ እንደ ጥሩ መሪ ዎች አይተው ያከብሩናል::

7ኛ ጥያቄ:- ሀ) በብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ማዘግየት የሚታይባቸውን ሌሎች መንገዶች ግለጽ:: ለ) ነገሮችን ማዘግየት የቤተ ክርስቲያን መሪን ውጤታማነት የሚገድበው እንዴት ነው?

ለ. ነገሮችን የማዘግየት ዝንባሌያችንን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል:-

1) <u>ራስህን መግዛት ተማር</u>:: ይህ ከመንፈስ ፍሬ አንዱ ነው:: (ገላ. 5:23፣ ምሳሌ 25:28፣ 2ኛ ጴጥ. 1:6 አንብብ::) ራስን መግዛት ማለት ስሜታችንን በመቆጣጠር የምንፈልገውን ሳይሆን ትክክል ነው ብለን የምናምነውን ተግባር መፈጸም ማለት ነው:: ራሱን የሚገዛ ሰው እሠራለሁ ያለውን ተግባር በማከናወን ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል:: ለምሳሌ፣ ራሱን የሚቆጣጠር ሰው በሰዓቱ ከቢሮው ለመድረስ መስማማቱን ስለሚያውቅ፣ ሰዓቱን አክብሮ ከሥራ ቦታው ላይ ይገኛል:: ራሱን የሚገዛ መሪ አመራር ለእግዚአብሔር ሕዝብ ምሪት መስጠትን እንደሚያካትት ስለሚያውቅ፣ የበለጠ ለማከናወን ደስ የሚያሰኙት ሌሎች ነገሮች



ቢኖሩም እንኳን፣ ለቤተ ክርስቲያን ራእይ እንደ መንደፍ ባሉት ከባድ ሥራዎች ላይ ጊዜውን ያሳልፋ::

2) ከሥራ ቦታህ ከመድረስህ በፊት ለማከናወን የምትፈልጋቸውን ተግባራት ዝርዝር መያዝህን አረጋግጥ:: ቢሮህ እንደ ደረስክ ምን እንደምትሠራ እወቅ:: ቢሮህ እንደ ደረስክ ወዲያውኑ ሥራህን ጀምር::

3) የጊዜ ሠሌዳህን ስታዘጋጅ አስፈላጊና ዳሩ ግን አጣዳፊ ያልሆኑ ነገሮች ቅድሚያ ማግኘታቸውን አረጋግጥ:: አንድ መሪ ለአንድ ነገር ቅድሚያ የሚሰጠው ከሦስት ነገሮች አንጻር ነው::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ኃላፊነቶቹን በመመልከት፣ «እግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያን የሰጡኝን ኃላፊነቶች ለማከናወን እንደ መሪ ሳደርግ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሌሎችን ሳልወክል እኔው ሳደርግ የምችላቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው?» የሚል ጥያቄ መጠየቅ አለበት::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሊያከናውን የሚገባቸውን ነገሮች በመመልከት፣ «ለቤተ ክርስቲያንና ለእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?» የሚል ጥያቄ ማንሣት አለበት:: መሪው ትኩረት ማድረግ ያለበት በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ለውጥ በሚያመጡ ነገሮች ላይ እንጂ፣ እስከዚህም ጠቃሚ ባልሆኑት ነገሮች ላይ መሆን የለበትም::

<u>ሦስተኛ</u>፣ እግዚአብሔር ስጦታ የሰጠውና ለማከናወን ደስ የሚያሰኙት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? የመሥራት ኃይላችንን ለማደስ የግድ መከናወን ያለባቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ደስ የሚያሰኙ ንን ነገሮች ጭምር ማከናወን ይኖርብናል::

4) <u>አንድ ሰው አስፈላጊ ተግባራት ማከናወንህን በኃላፊነት እንዲጠይቅህ አድርግ</u>:: ለጓደኛህ ወይም ለሌላ ሽማግሌ፣ «ይህን ሪፖርት እስከ እርብ ዕለት ማጠናቀቅ አለብኝ:: ረቡዕ ዕለት ግማሽ ያህል መሥራት አለመሥራቴን ጠይቀኝ፣» በል:: አንድ ሰው እንደሚጠይቀን ስናውቅ፣ ተግተን እንሠራለን:: ለዚህ ነው አስተማሪዎች የጥናት ወረቀቶቻችንን በተወሰነ ቀን እንድናቀርብ

በሚጠይቁን ጊዜ፣ በተባለው ጊዜ የምናደርሰው:: አንድ የምናከብረው ሰው አንድን ሥራ ማከናወናችንን እንደሚጠይቅ ስናውቅ፣ ሥራውን በፍጥነት ለመፈጸም እንነቃቃለን::

5) <u>ትልልቅ ሥራዎችን በአነስተኛ ክፍሎች ከፋፍል</u>:: ከምንዘገይባቸው ምክንያቶች አንዱ አንድ ነገር በጣም ትልቅና ከባድ በመሆኑ ምክንያት የቱ ጋ እንደምንጀምር ስለሚጨንቀን ነው:: ይህንን ስሜት ለማስወገድ ትልቁን ነገር በትናንሽ ክፍሎች መከፋፈል አለብን:: ከዚያም በየቀኑ ከክፍልፋዮቹ አንዱን እንሠራለን:: እያንዳንዱን ክፍልፋይ ስትጨርስ፣ ትልቁን ሥራ ወደ ማጠናቀቁ እንደምትቃረብ ስለምታውቅ፣ ቀጣዩን ክፍልፋይ ለማከናወን ትነቃቃለህ::

6) <u>በአገልግሎትህ ድፍረት እንድታገኝ የሚያግዙህን ነገሮች አድርግ</u>:: አንድን ነገር የማናደርግበት ሌላው ምክንያት ብቃት ያለን ስለማይመስለን ነው:: ለጎረቤቶቻችን የመመስከር ኃላፊነት እንዳለብን እናውቃለን:: ነገር ግን ይህን የማድረግ ብቃት ያለን አይመስለንም:: ስለዚህ ድፍረት ለማግኘት የሚያስችሉንን ነገሮች ማድረግ አለብን:: ይህ ምናልባት መጻሕፍት በማንበብ ወይም የሌላ ሃይማኖት ተከታዮችን እንዴት በወንጌል መድረስ እንደሚቻል የሚያስረዱ ሥልጠናዎችን በመከታተል፣ ልምድ ያለው ወንጌላዊ ሲመሰክር በመመልከት፣ የትልልቅ ሰዎችን ያህል ከማያስፈራ ትንሽ ልጅ ጋር በመነጋገር፣ ወዘተ. . . ሊገኝ የሚችል ነው:: በትናንሽ ነገሮች ድፍረት እያገኘህ ስትሄድ፣ አስቸጋሪ ናቸው የምትላቸውን ትላልቅ ነገሮች ማከናወን ይቀልሃል:: (ለምሳሌ፣ ሰዎችን እንደ መጋፈጥ፣ ዕቅዶችን እንደ ማውጣት፣ ኮሚቴዎችን እንደ መርዳት፣ ወዘተ. . . ያሉ ከባባድ ሥራዎች በትናንሽ ክፍሎች ተከፋፍለው ሊከናወኑ ይችላሉ::)

7) <u>የችግሮችን ምንጭ ለማግኘትና በፍጥነት መፍትሔ ለመስጠት ሞክር</u>:: እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ እግዚአብሔር የለጠን የማንወዳቸው ነገሮች እንዳሉ ልናውቅ ይገባል:: ሁልጊዜም ችግሮች አሉ (ለምሳሌ፣ ኅሰኝነት፣ ኃጢአት፣ የፍቅር አለመኖር፣ ወዘተ. . . )፣ እነዚህን ችግሮች ቸል የምንል ከሆነ፣ በአብዛኛው



እያደጉ ይሄዳሉ:: ነገር ግን ችግሮቹ ገና እንደ ተከሰቱ ተገንዝበን መሠረታዊ ምንጫቸውን ለመረዳት ብንሞክር፣ ብዙውን ጊዜ መፍትሔ ልንሰጥ እንችላለን:: ሁሉንም ችግር ወዲያውኑ ላንፈታ እንችላለን:: ነገር ግን ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችሉትን አንድ ወይም ሁለት የፈጠራ ጥበብ የታከለባቸውን ነገሮች ልናከናውን እንችላለን::

2. በአገልግሎት ላይ እንዳናተኩር የሚያደርጉንን የግል ችግሮች አለማስወገድ::

በጥሩ ሁኔታ ለመሥራት እንድንችል፣ በምናከናውነው ተግባር ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን:: አእምሯችን እንዲዋዥቅ የሚያደርግ ማንኛውም ነገር ጊዜያችንን ያባክነዋል:: ምክንያቱም በሥራው ላይ ትኩረት አናደርግም:: እንዳንድ መሪዎች በአንድ ጊዜ ብዙ ሥራዎችን ማከናወን ቢችሉም፣ አብዛኞቹ መሪዎች በውጤታማነት ሊሠሩ የሚችሉት አንድ ጊዜ በአንድ ነገር ላይ ነው::

በምናከናውነው ተግባር ላይ ለማተኮር የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወሱ ጠቃሚ ነው:-

ሀ. <u>ትኩረት ማድረግ እንድትችል አሳብህን ከሚሰርቁ ነገሮች ራቅ</u>:: ኢየሱስ ሰዎች በሚፈልጉት ጊዜ ሁሉ አይገኝላቸውም ነበር:: አስፈላጊ በሆነው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ እንዲችል፣ ሰዎች ወደሌሉባቸው ቦታዎች ይሄድ ነበር:: ሰዎች ከአጠገቡ ሆነው እየተነጋገሩ፣ እየተሳሰቁና ጥያቄዎችን እየጠየቁት ውጤታማ ጸሎት ሊጸልይ እንደማይችል ያውቅ ነበር:: ስለዚህ ከሰዎች ተለይቶ ከእግዚአብሔር ጋር ያሳልፍ ነበር:: ሐዋርያትን እንደ መምረጥ ያሉትን ዐበይት ውሳኔዎች ከመስጠቱ በፊት፣ ብቻውን በጸሎት ያሳልፍ እንደ ነበረ እንረዳለን (ሉቃስ 6:1-16):: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድ መሪ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ ሙሉ በሙሉ ትኩረት ለማድረግ እንዲችል ብቻውን የሚሆንበት ጊዜ ሊኖረው ይገባል::

ነገር ግን፣ እዚህ ላይ መሪዎች ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ሰዎች እኛን ለማግኘት ፈልገው የማያገኙን ከሆነ፣ ስሜታቸው ሊጎዳ

ይችላል። የሚከተሉትን ነገሮች ብናደርግ፣ ሰዎች ለጠቃሚ አገልግሎቶች የጽሞና ጊዜ መውሰዳችንን አይቃወሙም:-

1) የልባችን ፍላጎት ትክክል ሊሆን። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች፣ ሥራችን ሰዎችን መርዳት ነው። ለእነርሱ አገልግሎት ካልሰጠን፣ «ከሰዎች የራቅሁት ለራሴ ምቾት ስል ነው ወይስ ሰዎችን ሊሰውጡ ወይም ሊረዱ በሚችሉ ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በበለጠ እንዳገለግል ነው?» የሚል ጥያቄ ማንሣት አለባቸው። ከሰዎች መራቅ ያለብን የበለጠ ልናገለግላቸው እንድንችል እንጂ፣ ከማይመቹን ነገሮች ገለል ለማለት መሆን የለበትም።

2) ከሰዎች ጋር በምንሆንበት ጊዜ ሙሉ ትኩረታችንን ልንሰጣቸውና በቀረበው ጉዳይ ላይ በሚገባ እጽንአት መስጠት አለብን። ሰዎች ከእንተ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ ሌሎች ነገሮች አሳብህን እንዲያቋርጡ ማድረግ የለብህም። ለምሳሌ፣ ስልክ ማነጋገር ወይም በጠረጴዛህ ላይ ያሉትን ወረቀቶች ማገላበጥ የለብህም። ሰዎች ከአንተ ጋር በነበራቸው ቆይታ ሙሉ ትኩረትህን እንደ ሰጠሃቸው ካወቁ፣ ቶሎ ጉዳያቸውን ጨርሰው ሊሄዱ ይችላሉ።

3) ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ መሥራትህን በማይቀንስ መንገድ ከሰዎች ጋር ጊዜ የምታሳልፍበትን መንገድ ፍጠር። ለምሳሌ፣ ድንገተኛ ጉዳዮች እስካልተከሰቱ ድረስ፣ አንድ መጋቢ ጠዋት ከሰዎች ጋር አይገናኝም። እሑድ ጠዋት ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ከሰዎች ጋር ይገናኛል። የሁሉንም አባላት ስም ስላጠና፣ በስማቸው አየጠራ ሰላምታ ይሰጣቸዋል፤ እንዴት እየተመላለሱ እንደ ሆነም ይጠይቃቸዋል። ከፕሮግራሙ በኋላም ወደ ኋላ ቀርቶ ከሰዎች ጋር ይነጋገራል። በዚህ ዓይነት ሰዎች ለእርሱ አስፈላጊዎች መሆናቸውን ያሳያል። ስለዚህ ሰዎች ሊያገኙት ፈልገው እንደማይመቸው በሚነገራቸው ጊዜ ስሜታቸው ሳይጎዳ ከሰዓት በኋላ ቀጠሮ ለመያዝ ይስማማሉ።



8ኛ ጥያቄ:- ሥራ የሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ ብዙ ማሰብ በሚጠይቁ አስፈላጊ ነገሮች ላይ ትኩረት አያደረገ ሰዎች በሚፈልጉት ጊዜ ሊያገኛቸው የሚችልባቸውን ፈጠራ የታከለባቸውን ዘዴዎች ግለጽ።

ሰ. በሥራችን ላይ ለማተኮር እንድንችል ለስሜታዊነት የሚገፋፉንን ነገሮች ማስወገድ። በልባችን ውስጥ ቁጣ፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ወይም የበደለኝነት ስሜት በሚኖርበት ጊዜ፣ ውጤታማ ተግባር ለማከናወን አንችልም። ሁላችንም አጅግ ያዳከሙንና በሥራችን ላይ ትኩረት እንዳናደርግ ተጽዕኖ ያሳደሩብን ነገሮች አጋጥመውናል። ለምሳሌ፣ ከትዳር ጓደኛችን ጋር ልንጣላ እንችላለን። በዚህ ጊዜ በሥራ ቦታችን ላይ በምንሆንበት ጊዜ፣ አሳባችን በሥራችን ላይ ከማተኮር ይልቅ ወደ ጸቡ እየሸፈተ ሊያስቸግረን ይችላል። ወይም ደግሞ ከሥራ ባልደረባችንና ከሌላ ሽማግሌ ጋር ተጋጭተን ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ነገሮች በሚያውኩን ጊዜ፣ ውጤታማ ሥራ ማከናወኑ እስቸጋሪ ነው። ስሜታችን ከሥራችን እንዳያዘናጋን የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይኖርብናል:-

1) <u>የግንኙነት ጉዳዮችን በተቻለ ፍጥነት</u> አስተካ<u>ክል</u> (ትምህርት 14 እና 15ን ተመልከት።) የእግዚአብሔር ቃል እንደ ተቆጣን ፀሐይ እንዳትገባብን ያዝዘናል (ኤፌ. 4:26)። ይህ ማለት በተቻለ ፍጥነት ለጸብ የገፋፉንን ነገሮች ማስተካከል አለብን ማለት ነው። ይህ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን፣ በሥራችን ላይ በማተኮር የበለጠ ውጤታማ እንድንሆንም ያስችለናል።

2) <u>ከጓደኞችህ፣ ከባለቤትህና ከልጆችህ ጋር በፍቅር የደመቀ ግንኙነት እንዲኖርህ አድርግ</u>። ብዙም ከማናውቃቸው ሰዎች ጋር የግንኙነት ችግሮች ቢገጥሙን፣ ያን ያህል ከባድ ችግር ላይሆን ይችላል። ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ከተበላሸ ግን፣ የበለጠ ሁኔታው አስቸጋሪ ይሆንብናል። ስለሆነም ከጓደኞቻችን፣ ከትዳር ጓደኞችንና ከልጆቻችን ጋር በሰላም የምንኖርበትን መንገድ መፍጠር አለብን።

3) ከመጠን በላይ በአገልግሎት እንዳትጠመድ ወይም እንዳትዳከም ተጠንቀቅ:: ቶሎ ቶሎ እንድንቆጣ ወይም በትናንሽ ነገሮች እንድንበሳጭ ከሚያደርጉን ነገሮች አንዱ በሥራ ብዛት መዛል ነው:: እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ከመጠን በላይ በመሥራታችን እንዳከማለን:: ስለሆነም አላስፈላጊ ከሆኑ ሥራዎች ራሳችንን ማራቅ አለብን፤ ማረፍም አለብን:: ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በሳምንት ስድስት ቀናት የሚሠራ ሰው ሰባቱንም ቀናት ከሚሠራ ሰው በላይ ውጤታማ ነው:: ለዚህም ምክንያቱ በሳምንት ሰባት ቀናት በምንሠራበት ጊዜ ስሜታዊ ዝለት ስለሚገጥመን፣ በምናከናውነው ተግባር ላይ እምብዛም ትኩረት ልናደርግ አንችልም:: ነገር ግን እረፍት በምናደርግበት ጊዜ፣ በሥራችን ላይ በበለጠ ትኩረት ለማድረግና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስሜታዊ ብቃት ይኖረናል:: ለዚህ ነው እግዚአብሔር አይሁዶች በሳምንት አንድ ቀን እንዲያርፉ የነገራቸው (ዘጸአ. 20:8-11)::

| |
|---|
| 9ኛ ጥያቄ:- ሀ) የሚረብሹ ነገሮች በሥራህ ላይ እንዳታተኩር ሲያደርጉ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙውን ጊዜ በሥራቸው ላይ እንዳያተኩሩ የሚያደርጉ ምን ዓይነት ነገሮች ይገጥሟቸዋል? ሐ) በሥራው ላይ እንዳያተኩር የሚያደርግ ስሜታዊ ችግር ላለበት መሪ ምን ዓይነት ምክር ትሰጠዋለህ? |

3. በሁሉም ነገሮች ውስጥ ሰመሳተፍ ከመጣር ተቆጠብ:: እግዚአብሔር አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ብዙ ጊዜ እንዲያገኝ ያቀደው በውክልና ሂደት መሆኑን አስታውስ:: (ስለ ውክልና ትምህርት 11ን ተመልከት::) እንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውክልና ለመስጠት የሚከተሉትን ነገሮች መማር አለበት::

ሀ. ሁሉንም ነገር መቆጣጠር አለብኝ የሚል እሳብ ሊኖረን አይገባም:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሁሉንም መሆን አለብኝ የሚል ወይም ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠር ከሆነ፣ አስፈላጊ ነገሮችን ለማከናወን የሚያስችል ጊዜ ሊያገኝ አይችልም:: አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉንም ነገር ለማከናወን ይፈልጋሉ:: ስኳርና ሻይ ቅጠል መግዛት፣ ደብዳቤዎችን መጻፍ፣ ሁሉንም ገንዘብ



መቆጣጠርና ለትንሽ ገንዘብ ሳይቀር ሰዎች ወደ እነርሱ እንዲመጡ የማድረግ ፍላጎት አላቸው:: ውክልና በምንሰጥበት ጊዜ፣ ነገሮችን መቆጣጠራችንን በመተው ሌሎች አንዳንድ ውሳኔዎችን እንዲሰጡ ማድረግ መፍቀድ አለብን::

ለ. ሰዎች ችግሮቻቸውን ለመፍታት ከሌላ ሰው ይልቅ ወደ እኛ መምጣታቸው የእኛን አስፈላጊነት ይጨምራል ከሚል አሳብ መራቅ አለብን:: ድብቅ ለመሆን ካልፈለግን በቀር፣ ብዙዎቻችን ወሳኝ ሰው ሆነን ለመታየት እንደምንፈልግ ግልጽ ነው:: ሰዎች ለትንሽ ነገር ወደ እኛ ሊመጡና ችግሩን ስንፈታላቸው፣ የተፈላጊነት ስሜት ይሰማናል:: «እያችሁ፣ ይሄ ሁሉ ሰው ችግሩን ለመፍታት የእኔ ርዳታ ያስፈልገዋል፣» የሚል ስሜት ይሰማናል:: ውክልና መስጠት ማለት ለሰዎች ችግር መፍትሔ መሆናችንን ማቆም ማለት ነው:: ሌሎች ውሳኔዎቹን እንዲሰጡ እናደርጋለን ማለት ነው::

ሐ. ሌሎች ከእኛ በተሻለ መንገድ የሚሠሯቸውን ነገሮች ከማድረግ እንቆጠባለን:: ታማኝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳቸው ጥሩ አድርገው የሚሠሯቸውና የማይሠሯቸው ነገሮች መኖራቸውን ይረዳሉ:: እያንዳንዳችን ጥሩ ሰባኪ መሆን አለመሆናችንን እናውቀዋለን:: ጥሩ ሰባኪዎች ካልሆንን፣ ሌሎች ሰዎች እንዲሰብኩ ማድረግ ነው ያለብን:: በገንዘብ አያያዝ ጎበዝ ካልሆንን፣ ሌላ ሰው ይህንን ኃላፊነት እንዲወጣ ማድረግ አለብን:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ አግዚአብሔር መንግሥት የሚያስብ ከሆነ፣ ነገሮችን መቆጣጠር አለብኝ ሳይል ችሎታው ያላቸው ሰዎች እንዲያከናውኑት ያደርጋል::

መ. የቤተ ክርስቲያን መሪ የወከልኩት ሰው ሊወድቅ ይችላል ከሚል ፍርሃት መውጣት አለበት:: የቤተ ክርስቲያን መሪውን ጨምሮ፣ ማንም ሰው ይወድቃል:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መሪው ግለሰቡ ሊወድቅ ወይም ጥሩ አድርጎ ሳይሠራ ይችላል የሚል ፍርሃት ካለበት፣ ሰዎችን ሳይወክል ይችላል:: ሰዎች ጥሩ ሥራ ሊሠሩ የሚችሉት ስናምናቸው ነው:: እወድቃለሁ የሚል ፍርሃት ካለባቸው ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ደስ አይሰኝብኝም

የሚሉ ከሆነ፣ ተግተው ሊሠሩ ወይም አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ሊሰጡ አይችሉም:: ከዚህ ይልቅ፣ ጥቃቅን ችግሮችን ይዘው ወደ መሪ በመሄድ እሁንም የቤተ ክርስቲያን መሪው ሁሉንም ነገር እንዲያደርግ ሊያጨናንቁት ይችላሉ:: መሪዎች ሰዎችን ሊያሠስጥኑና መመሪያዎችን ሊሰጧቸው ይገባል:: ችግሮች በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ አጋጣሚውን በመጠቀም በሚቀጥለው ጊዜ እንዴት የተሻለ ሥራ ማከናወን እንደሚቻል ሊያስተምሩ ይችላሉ:: አንድ መጋቢ የአመራር ዓላማውን አስመልክቶ ሲናገር፣ «ትክክለኛ ሰዎችን መመልመልና የብቃት ስሜት እስኪሰማቸው ድረስ ማሠልጠን» ነው ብሏል::

4. እሳስፈላጊ ሥራዎችን «አልሠራም» ማለት አለብን:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሳስፈላጊ ሥራዎችን ከሚሠሩባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰዎች ምን ይሉኛል? በሚል እሳብ ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ከሩቅ ቦታ መጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄደን አንድንሰብክ ይጠይቀናል:: «የአንድ ሰዓት ስብከት ብቻ ነው፣» ሲልም ያግባባናል:: ነገር ግን ስብከቱን ለማዘጋጀት የሚፈጀውን ጊዜ፣ አስከ ቤተ ክርስቲያኑ ለመድረስ የሚወስደውን፣ እንዲሁም ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን የስሜት ውጣ ውረድ እሳንሰው ያያሉ:: ነገር ግን «አልችልም» ማለቱ ስለሚከብደን፣ «አሺ» እንላለን:: አሺ በምንልበት ጊዜ፣ ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ:: በመጀመሪያ፣ እግዚእብሔር እስፈላጊ የሆነውን ነገር አንድናከናውን የሰጠንን ጊዜ ሌሎች ሰዎች አንዲወስኑልን እየፈቀድን ነው:: እግዚእብሔር የምናደርገውን ነገር እንዲወስን እላደረግንም:: ሁለተኛ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ አስፈላጊውን ነገር «አሳደርግም» አያልን ነው:: ነገሮችን ለማከናወን ያለን ጊዜ ውስን ነው:: እንዱን «እደርጋለሁ» ስንል ሌላውን «አላደርግም» አያልን መሆናችን ግልጽ ነው:: ይህ ደግሞ ሰዎች የጊዜ አጠቃቀማችንን እንዲወስኑ ማድረግ ነው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመጠን በላይ በሥራ መጠመድ እደገኛ መሆኑንም መገንዘብ አለባቸው:: ብዙውን ጊዜ ስጦታው ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቅ በቤተ ክርስቲያን



ቀጣና ይቀጠራል:: ሰዎች በተደጋጋሚ ወደዚህ ሠራተኛ ጥያቄዎችን ይዘው ይመጣሉ:: እነዚህ ጥያቄዎች፣ «የመጽሐፍ ቅዱስ እጠናን አስተምር፣ በቤተ ክርስቲያኔ ስበክ፣ እዚያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እየተጣሉ ስለሆነ ሄደህ አስታርቃቸው . . . » የሚሉ ይሆናሉ:: መሪው የሰዎችን ስሜት ሳይጎዳ «አልችልም» ለማለት ይቸገራል:: አልችልም ቢል ሰዎች ጥሩ ያልሆነ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ:: «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲገባ ገንዘባችንን ሰጥተን ነበር:: አሁን ግን ሊረዳን ፈቃደኛ አይደለም:: ማን ነኝ ብሎ ነው እንዲህ የሚያደርግ?» የሚሉ አሳቦች ሊመጡ ይችላሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምሩቁ ብዙ ሥራዎችን በሰጡ ቁጥር፣ እየዛለ ይሄዳል:: ብዙም ሳይቆይ እርሱ፣ ቤተሰቡና ሥራው ለችግር ይጋለጣሉ::

የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ ሳይዳከም አስፈላጊ ነው ተብሎ የታመነውን ተግባር አንዲያከናውን ለማስቻል ጥበቃ ማድረጉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነት ነው:: ምናልባትም ሁሉም የአገልግሎት ጥያቄዎች ወደ እነርሱ እንዲሄዱ ኪያደርጉ ይችላሉ:: ከዚያ በኋላ ከሠራተኛው ጋር በመሆን፣ ሀ) ግለሰቡ አጅግ በመድከም ውጤታማ ሳይሆን እንዳይቀር ጥንቃቄ ማድረግ፣ ለ) ለሠራተኛው የተሰጡት ዐበይት ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥና ሐ) ቤተሰቡ ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኝ ማገዝ እለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውድ ሠራተኞቻቸው ከሚገባው በላይ እንዳይሠሩ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሠራተኛው መሪዎቹ የሰጡትን ተግባር በእጥጋቢ ሁኔታ ለማከናወን ካለመቻሉም በላይ፣ ሥራውን በመተው መጠነኛ ኃላፊነት የሚጠይቅ ሌላ ሥራ ሊይዝ ይችላል:: ይህ በእንድ አህያ ላይ አምስት ኩንታል ጤፍ ጭኖ ወደ ገበያ ለመሄድ የመሞከርን ያህል የሞኝነት ተግባር ነው:: አህያው እስከ ግማሽ መንገድ ከሄደ በኋላ ሊወድቅ ይችላል:: በዚህ ጊዜ ማን ይሆን ጤፉን ወደ ገበያ የሚያደርሰው? በየጊዜው አህያው መሥራቱን እንዲቀጥል ተመጣጣኝ ጭነት ብቻ አንዲሸከም ማድረጉ ምንኛ ጠቃሚ ነበር:: ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች ከሚገባ በላይ እንዲሠሩ በማድረጋቸው አጥተዋቸዋል::

አንድ <u>የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ</u> ከመጠን በላይ ሥራ ሲበዛበትና አስፈላጊዎቹን ተግባራት ለማከናወን ሳይችል ሲቀር ምን ማድረግ ይችላል? አንዱ አማራጭ የሥራ ክንውኖቹን የሚያሳየውን የጊዜ ሠሌዳ ለሽማግሌዎች ስብሳቢ ማምጣት ሊሆን ይችላል:: በዚህ የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን እንዲያከናውን የሰጠችውን ኃላፊነቶች ጽፎአቸዋል:: እንዲያከናውን የሚጠየቃቸው ተጨማሪ ነገሮችም በዚህ የጊዜ ሠሌዳ ላይ ተ መልክተዋል:: አገልጋዩ እነዚህን ዝርዝሮች ለሽማግሌው በማሳየት፣ «እዚያ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ እንዳገለግል ከፈለግክ፣ ለሽማግሌዎች ስብሰባ ሪፖርት ሳዘጋጅ አልችልም:: ለአዳዲስ አማኞች እንዳስተ ምር የጠየቅከኝን የደቀ መዝሙርነት ትምህርትም ሳስተምር አልችልም:: ሪፖርቱን እንዳዘጋጅና አዳዲስ አማኞችን እንዳስተምር ትፈልጋለህ? ወይስ እዚያ ሄጄ ልሰበክ? ሁሉንም ነገር ሳደርግ አልችልም፤» ማለት አለበት:: ሽማግሌው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለአገልጋዩ ሊያሳውቅ ይችላል:: ነገር ግን ሽማግሌው አገልጋይ ምን እየሠራ እንዳለና የጊዜ ጥበትም እንዳለበት ካላወቀ፣ ለምን ለአገልግሎት ዕድሎች አሉታዊ ምላሽ እንደሚሰጥ ላይረዳ ይችላል::

> 10ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሠራተኞቹን በሥራ ለሚያጨናንቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ ምን ዓይነት ምክር ትሰጠዋለህ? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ በሥራ ብዛት ለሚያጨናንቃቸው ሠራተኞችስ ምን ዓይነት ምክር ትሰጣለህ?

5. በሥራ ብዛት ምክንያት እረፍት ለመውሰድ አለመፈለግ::

ክላይ እንደ ተመለከተው፣ እግዚአብሔር ሁሉም ሰው በሳምንት አንድ ቀን እንዲያርፍ ደንብ ክማውጣቱም በላይ፣ ሰዎች እረፍት አድርገው ራሳቸውን በሚያድሉበት ጊዜ የበለጠ ሥራ ለማከናወን ይችላሉ:: እረፍት በማናደርግበት ጊዜ በግልጽ አእምሮና በሙሉ ኃይላችን ለመሥራት ስለማንችል፣ ብዙ ጊዜ እናባክናለን:: ደክመን ሳለ ከመሥራት ይልቅ የተወሰነ እረፍት አድርጎ ራስን በማደስ በቀጣዩ ዕለት የተሻለ ሥራ ማከናወኑ ጠቃሚ ነው::

6. አንድ ሰው ምን ያህል የመሥራት ወይም ያለመሥራት ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ መመሪያ አለመስጠት::



በቢሮ ውስጥ ጊዜ ከሚያባክኑ ነገሮች አንዱ ማን በምን ምን ጉዳዮች ላይ ሥልጣን እንዳለው አለመታወቁ ነው:: ሽማግሌው ሠራተኛው የሰንበት ትምህርት ቤት ፕሮግራም የማዘጋጀት ኃላፊነት አለው የሚል ግምት ይኖረዋል:: ሠራተኛው ግን ሽማግሌ ው ይህ ኃላፊነት እንደሚመለከተው እንዲነግረው ይጠብቃል:: አንዱ ሌላውን እየጠበቀ ምንም ሥራ ሳይሠራ ይቀራል:: ይህ ደግሞ በአሳብ መተላለፍን ያስከትላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያደርጉ ከሚችሏቸው ነገሮች አንዱ ሠራተኞች ራሳቸው ምን ምን ዓይነት ውሳኔዎችን ሊያስተላልፉ እንደሚችሉና የትኞቹን ነገሮች ከእነርሱ በላይ ያለው ሰው ሊያጸድቅላቸው እንደሚገባ ግልጽ ማድረግ ነው:: ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች አንድ ነገር ባደርግ እሳሳት ይሆናል በሚል አሳብ ተይዘው ምንም ነገር ሳያከናውኑ ይኖራሉ:: አዳዲስ ሠራተኞች ምን ዓይነት ነገሮች ላይ ራሳቸው ሊወስኑና በምን ዓይነቶቹ ላይ የመሪዎችን ውሳኔ ሊጠብቁ እንደሚገባ መጠየቅ አለባቸው:: እነዚህን መመሪያዎች በትክክል ማወቅ፣ ሠራተኞች ሊያከናውኗ የሚችሏቸውንና ኃላፊነታቸው ያልሆኑትን ነገሮች ለይተው እንዲያውቁ ያስችላቸዋል::

7. ችግሮችን በፍጥነት ከመፍታት ይልቅ ቀውጢ ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ መጠበቅ

ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአንዱ «ቀውጢ» ሁኔታ ወደ ሌላው የሚሸጋገሩ ይመስላል:: ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪው ጊዜ ውን በአግባቡ ለመጠቀም አለመቻሉን የሚያሳይ ነው:: ይህ ነገሮች እስኪባባሱ ድረስ እንደሚጠብቅና በእንጭጩ ለመቅጨት እንደማይሞክር ያሳያል:: የችግሮቹን ምንጭ ባለማድረቁ ምክንያት ችግሮች በተደጋጋሚ መከሰታቸውንም ያሳያል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግሮችን መጀመሪያውኑ ከመፍታት ይልቅ ትልቅ ችግር እስኪፈጠር ድረስ ይጠብቃሉ::

8. ሥራው በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል በሚል ስሜት አለመርካት::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያጋጥሙ ሁለት ችግሮች አሉ:: በመጀመሪያ፣ ነገሮችን በጥራት ለማከናወን ያለመጨነቅ ችግር አለ:: ስለዚህ፣ አንዳንድ መሪዎች ሪፖርት እስከ ተዘጋጀ ድረስ (ትክክል ባይሆንም)፣ በቂ ነው ብለው ያስባሉ:: ይህ ሁሉንም ነገር እርሱን በሚያስከብር መንገድ እንድናከናውን ለሚጠይቀን አምላካችን ስድብ ነው:: (1ኛ ቆሮ. 10:31ን አንብብ::)

ሁለተኛ፣ ሌሎች መሪዎች ደግሞ ምንም አይረኩም:: ስለዚህ ደብዳቤው ውስጥ አንዲት ስሕተት ካለች፣ እንደገና ይጽፉታል:: ይህ «ፍጹማዊነት» የሚባል ሲሆን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጊዜያቸውን እንዲያጠፉ የሚያደርግ ነው:: ሁልጊዜም አንድን ነገር ማሻሻል የሚቻልባቸው መንገዶች አሉ:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ አንድ ነገር የታሰመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የሚያስፈልገውንና ምርጥ እድርጎ መሥራትን ማወቅ አለበት:: እንዳንድ ሰባኪዎች አንድ ስብከት ለማዘጋጀት እራት ሰዓታት ያጠፋሉ:: ብዙውን ጊዜ ግን ስድስት ሰዓት የፈጀው ዝግጅትና ስምንት ሰዓት የፈጀው ዝግጅት በሰዎች ልብ ውስጥ የሚያመጣው ለውጥ አንድ ዓይነት ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ የተሠራ ሠንጠረዥ በሁለት ሰዓታት የተሠራውን ውስብስብ ሠንጠረዥ ያህል በቂ መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል::

በእመራር ውጤታማነት የሚገኘው አንድን ነገር ጥሩ አድርጎ ባለመሥራትና ፍጹም ባለመርካት መካከል ያለውን ሚዛናዊነት በመጠበቅ ነው:: እግዚአብሔር የስጠንን ሥራ ባስን ጊዜ ውስጥ ምርጥ እድርገን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለብን::

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ:- ሀ) በእነዚህ ስምንት መንገዶች ጊዜ የሚያባክኑ መሪዎችን እንዴት እንደ ተመለከትክ ግለጽ:: ለ) ሌሎች መሪዎች ጊዜ የሚያጠፉባቸውን መንገዶች ዘርዝር:: ሐ) በዚህ ሳምንት ጊዜህን እንዴት እንዳሳለፍክ ግለጽ:: የሚያስቸግሩህ የጊዜ ማባከኛ መንገዶች ምን ምንድን ናቸው? መ) በሚቀጥለው ሳምንት እግዚአብሔር የሰጠህን የጊዜ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ምን ታደርጋለህ? |



## ሦስተኛ ቀን

ጌታመሳይ የቤተ ክርስቲያኑ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ እንዲሆን ተመርጦ ነበር:: ቤተ ክርስቲያኑን በመንፈሳዊ መንገድ ለማገልገል ይጥር ነበር:: የተከበረ ሰው በመሆኑ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ የሚቀመጠው እርሱ ቤት ነበር:: በየሳምንቱ እሑድ እሑድ በመባና ምጽዋት የሚሰበሰበው ገንዘብ ይሰጠውና በተቆለፈ ሳጥን ውስጥ ይከትተዋል:: ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ከሳጥኑ ውስጥ አውጥቶ ይጠቀም ነበር:: አንድ ጊዜ ወጣቶች ጊታር ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ አሰባሰቡ:: ገንዘቡ ጊታሩን ለመግዛት ባለመብቃቱ ተጨማሪ ገንዘብ እስኪገኝ ድረስ ጌታመሳይ ዘንድ እንዲቆይ ሰጡት:: እርሱም ሌላው የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ባለበት ሳጥን ውስጥ ጨመረው:: በሚቀጥለው ወር ለወንጌላውያን ደመወዝ ለመክፈልና ለቀጣና ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋጮ ለመክፈል የሚያስችል በቂ ገንዘብ አልተሰባሰበም ነበር:: ጌታመሳይ ይህንን ሳይረዳ፣ ሳጥኑን ከፍቶ ለወንጌላውያን ደመወዛቸውን ከፈለ:: ከዚያም ወጣቶቹ ለጊታር መግዣ ያስቀመጡትን ገንዘብ እንዲሰጣቸው ጠየቁት:: ገንዘቡን ሲቆጥር፣ ለጊታሩ መግዣ የሚበቃ አልሆነም:: በዚህ ጊዜ ወጣቶቹ ተናድደው ገንዘባችንን ሰረቀብን ብለው ተናገሩ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ጌታመሳይ ገንዘቡን ሰረቀ ብለው አስወሩ:: ምንም እንኳን እርሱ እንደዚያ ባያደርግም፣ ከዚያ በኋላ ሰዎች ጌታመሳይን ማመን አቆሙ:: ሰዎችም ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በልግስና መስጠታቸውን ቀነሱ::

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ጥሩ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት አለመዘርጋቱ በጌታመሳይ ላይ ለምን ችግር እንዳስከተለ ግለጽ:: ለ) ገንዘብን በአግባቡ አለመቆጣጠር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮችን ሲፈጥር የተመለከትክበትን ሁኔታ አብራራ:: ሐ) ማቴ. 25:14-30፤ 1ኛ ቆሮ. 4:1-5ን አንብብ:: እግዚአብሔር የሰጠንን ሀብት በጥበብ እንድንጠቀም መፈለጉን እነዚህ ጥቅሶች የሚያሳዩት እንዴት ነው? |

እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥና አማኝነት ማድረግ የሚፈልገውን ተግባር በተመለከተ ራእይ በሚሰጠን ጊዜ፣ ሁልጊዜ

ም ይህንን አገልግሎት ለማሳካት የሚያስችል ሀብት ይሰጠናል። እግዚአብሔር ለሰጠን ሥራ ማከናወኛ በቂ ሀብት የለንም የምንል ከሆነ፣ ብዙውን ጊዜ አራት ችግሮች አሉ።

<u>አንደኛ</u>፣ በአመዛኙ ከእግዚአብሔር ያልሆነ ፍላጎት ይኖረናል። ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት የመምሰል ወይም ለራሳችን ክብርን የማግኘት ፍላጎት ይኖረናል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ሳይሆን፣ ራሳችን የምንፈልጋቸውን ነገሮች እናደርጋለን። እግዚአብሔር ሀብትን የሚሰጠን ራሱ ለሚፈልጋቸው ነገሮች እንጂ፣ እኛ ለምንፈልጋቸው ነገሮች አይደለም።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ጊዜው ገና የእግዚአብሔር ጊዜ ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር አሁን ሳይሆን ወደፊት እንድናደርጋቸው የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ነገሮች እኛ በምንፈልገው ፍጥነት. ሳይከናወኑ ሲቀር ትዕግሥት እናጣለን። ለምሳሌ ያህል፣ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ገና የ5 ዓመት እድሜ ጨቅላ ሆና ሳለ፣ 50 ዓመታት ካስቆጠረችው ቤተ ክርስቲያን እኩል ታላቅ እንድትሆንልን እንፈልጋለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ አብያተ ክርስቲያናቱ ደረጃ በደረጃ እንዲያድጉ ነው የሚፈልገው። ይህን የእድገት ሂደት ልናፋጥን አንችልም። እግዚአብሔር ብቻ ነው በራሱ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን የሚያሳካው። እናም ይህንን ጊዜ መጠበቅ አለብን።

<u>ሦስተኛ</u>፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ አማካኝነት ለማከናወን የሚፈልገውን ተግባር ለመፈጸም ሕዝቡን አናንቀሳቅስም። መሪዎች በአብዛኛው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ያለውን ራእይ ለምእመናን በማስተላለፉ በኩል የተሳካ ሥራ አይሠሩም። ስለዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ሥራ ደስ አይሰኙም። በመሆኑም፣ ራሳቸውንና ገንዘባቸውን ለሥራው አይሰጡም። በዘጸአት 35:30-36:7 ሕዝቡ እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በመካከላቸው ለማደር በመፈለጉ እጅግ እንደ ተደሰቱ እንመለከታለን። ለዚህ ሥራ አይሁዶች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ክህሎቶችና ገንዘባቸውን ከሚገባው በላይ



በመስጠታቸው በቃችሁ ተብለው ነበር። ዛሬም ተመሳሳይ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። የእግዚአብሔር ሕዝብ የእርሱን ራእይ በሚገባ በሚረዱበት ወቅት ጊዜያቸውን፣ ክህሎታቸውንና ገንዘባቸውን በመስጠት የሥራው አካል ለመሆን ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጠውን ራእይ ሰመፈጸም እንዲነሣሣ ለማድረግ የአሳብ ልውውጥን ክህሎት ይጠቀማል።

<u>አራተኛ</u>፣ መሪዎች እግዚአብሔር ለሥራው የሰጣቸውን ሀብት በአግባቡ አያስተዳድሩም። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸው ሁለት ዓይነት ዐበይት ሀብቶች አሉ። በዋናነት ለሰዎች ክህሎቶችንና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል። ምእመናን እግዚአብሔር እንዲሳተፉ በሚፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ በፈቃደኝነት መሳተፍ አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ ምእመናን ክህሎቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያውሉ ለማስቻል የአገልግሎት በሮችን መክፈታችንን ማረጋገጥ አለብን። ባለፈው ሳምንት ስለዚህ ክህሎት አጥንተናል። ይህም ሰዎች በእግዚአብሔር ሥራ ላይ እንደ ቡድን እንዲሠሩ ማስቻል ነው። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ለሰዎች ገንዘብን በመስጠት ለሥራው እንዲያውሉት ያደርጋል። ዛሬ በአግባቡ ገንዘብ የማስተዳደርን ክህሎት እንመለከታለን።

መሪዎች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኖቻችን ሊያደርግ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማከናወን ከፈለግን፣ የእነዚህ ሁለት ሀብቶች ጥሩ ባለ አደራዎች መሆን አለብን። እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲያስተዳድሯቸው ሰዎችንና ገንዘብን ሰጥቷቸዋል። እነዚህን ሀብቶች በየትኛውም መንገድ አላግባብ ብንጠቀም እንጠየቃለን። እግዚአብሔር የሚሰጠንን ሀብት በአግባቡ ሳናስተዳድር ስንቀር፣ ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ። <u>በመጀመሪያ</u>፣ እግዚአብሔር ይቀጣናል። እግዚአብሔር የሰጠውን ችሎታ በአግባቡ ያልተጠቀመ አስተዳዳሪ እንደሚቀጣ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ጥቅም እንድናውል የሰጠንን ሀብቶች ለተጠቀምንበት መንገድ ተጠያቂ ያደርገናል። <u>ሁለተኛ</u>፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ሀብቶች እናጣለን። እግዚአብሔር የሰጠንን የሰው ወይም የገንዘብ

ሀብት በአግባቡ በማንጠቀምበት ጊዜ፣ ሰዎች የበለጠ ፍሬያማ አገልግሎት ወደሚሰጡ አብያተ ክርስቲያናት ይሄዳሉ:: ወይም ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ መስጠታቸውን ያቆማሉ:: ሰዎች በመሪ ዎች የገንዘብ አጠቃቀም ላይ እምነት ካጡ፣ መስጠት ያቆማሉ:: መስጠት ካቆሙ በኋላ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናንን አንደገና ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ገንዘብ እንዲሰጡ ለማድረግ ይቸገራሉ:: ልክ እንደ ጌታመሳይ፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ በመሰረቃቸው ሳይሆን፣ በአግባቡ ገንዘቡን ለማስተ ዳደር ባለመቻላቸው የሕዝቡን እመኔታ ያጣሉ:: ጥሩ የገንዘብ አያያዝ አለመኖር ወደ ብዙ ችግሮች ሊመራ ይችላል:: ገንዘብን በአግባቡ ለማስተዳደር፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ እንዴት ለእግዚአብሔር ሥራ እንደ ዋለ የሚቆጣጠሩበትን ክህሎት ማዳበር አለባቸው::

13ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን በአግባቡ ባለማስተ ዳደራቸው፣ ስጦታ ያላቸው ምእመናን ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሄዱበትንና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ለመስማራት ያልቻ ሉበትን ሁኔታ አብራራ:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰዎችን መንፈሳዊ ስጦታዎች ለማስተዳደር ምን የተሻለ ተግባር ሊፈጽሙ ይችሉ ነበር? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ በአግባቡ ለማስተዳደር ባለመቻላቸው ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ሳይከናወኑ የቀሩበትን ሁኔታ ግለጽ:: መ) ይህ ችግር ሰዎች ለእግዚአብሔር ሥራ በፈቃደኝነት እንዳይሰጡ የሚያደርገው እንዴት ነው?

## ክህሎት አሥራ አንድ:- የገንዘብ ሀብትን በአግባቡ ማስተዳደር

### የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አጠቃቀም አጠቃላይ መርሖዎች

ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር ሀብት ባለ አደራዎች ናቸው ብሏል:: ሀብቱን በሚጠቀሙበት ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር ታማኝነትን እንዲያሳዩ ይፈልጋል (1ኛ ቆሮ. 4:1-5):: ታማኝ የእግዚአብሔር ሀብት ባለ አደራዎች ለመሆን ከፈለግን፣ ስለ ገንዘብ አስተዳደር የሚከተሉትን መርሖዎች ልብ ማለት ይኖርብናል:: (ማስታወሻ:- በመጽሐፍ አንድ ክፍል አንድ ውስጥ



ይህንን በተመለከተ በስፋት ስላጠናን፣ ከዚህ በታች ጠቅለል ያሉ ሐሳቦችን ብቻ እናቀርባለን::)

እግዚአብሔር ለሥራው እንጠቀምበት ዘንድ ገንዘብ ይሰጠናል:: ሁላችንም ለእግዚአብሔርና ለሥራው ለመስጠት እንችል ዘንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በገንዘብና በሥራ ላይ ያለውን እመለካከት ለምእመናን ማስተማር አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን ሁለት ነገሮችን ማስታወስ አለባቸው:-

<u>አንደኛ</u>፣ በቀዳሚነት እግዚአብሔር የሚባርክን ሀብታችንን ለመንግሥቱ እንድናውል ነው:: (መዝ. 67:1-2፣ 7 አንብብ::) በእመዛኙ የእግዚአብሔርን በረከቶች የምንመለከተው በራስ ወዳድነት ፍላጎት ነው:: አካላዊ በረከትን እንድናገኝ ብቻ እግዚአብሔር እንዲባርከን እንፈልጋለን:: ትልቅ ቤት እንዲኖረን ወይም ቴፕ እንድንገዛ የሚያስችል ጥሩ ሥራ እንዲሰጠን እንፈልጋለን:: ዳዊት ግን እግዚአብሔር የሚባርከን ለሌሎች በረከት እንድንሆን በማሰብ መሆኑን ተረድቶ ነበር:: ስለሆነም እርሱንና እስራኤላውያንን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲባርካቸውና እነርሱም በተ ራቸው ለሕዝብ በረከት እንዲሆኑ ጸለየ:: ምእመናን ሕይወታቸውንና ሀብታቸውን ለሌሎች በረከቶች የሚሆኑባቸው መንገዶች አድርገው በሚመለከቱበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥራውን ለማስፋት ይችላል::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ለሌሎች፣ በተለይም ለእግዚአብሔር የምናካፍለው እንዲኖረን (ኤፌ. 4:28፤ 1ኛ ተሰ. 4:11-12) ተግተን መሥራት አለብን:: እንደ ተሰሎንቄ ሰዎች ሁሉ ብዙዎቻችን መሥራት አንወድም:: የሚፈልጉትን ዓይነት ሥራ እስኪያገኙ ድረስ፣ ሥራ የማይሠሩ ብዙ ወጣቶች አሉ:: እነዚህ ወጣቶች ሌሎች ጥረው ያገ ኙትን ተጋርተው ለመኖር ይመርጣሉ:: ጳውሎስ ሊሠራ የሚችል ሰው ሁሉ መሥራት እንዳለበት አስገንዝቧል:: የማይሠሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን መቀጣት ያስፈልጋቸው ነበር (2ኛ ጢሞ. 3:6-15):: ጳውሎስ ከምንሠራባቸው ምክንያቶች አንዱ ሌሎችን ለመርዳት የሚያስችል ገንዘብ ለማግኘት መሆኑን ተናግሯል::

## 2. ገንዘቡ የእግዚአብሔር እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያን አይደለም።

14ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ገንዘብ ሁሉ የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ አለመሆኑን መረዳት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘቡን እንደ ፈለግን መጠቀም እንችላለን የሚል አመለካከት በሚኖራቸው ጊዜ ምን ይከሰታል? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ትክክለኛ ባልሆኑ ነገሮች ላይ በማዋል ሊያባክኑ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

መባ፣ አስራት ወይም ልዩ ስጦታ ቢሆን ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ገንዘብ የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ አለመሆኑን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማስታወስ አለባቸው። ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ገንዘብ አላግባብ መጠቀም የእግዚአብሔርን ገንዘብ አላግባብ መጠቀም ነው። የግል ገንዘባችንን አላግባብ መጠቀም አንድ ነገር ነው። በዚህ ጊዜ የምንችገረው ራሳችንና ቤተሰቦቻችን ብቻ ነን። የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ አላግባብ በምንጠቀምበት ጊዜ ግን፣ የእግዚአብሔርን ገንዘብ አላግባብ እየተጠቀምን ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከባድ ችግር ነው። ገንዘቡ የቤተ ክርስቲያን ነው ብለው በማለብ መሪዎች ለዘመዶቻቸው ወይም ለጓደኞቻቸው «ያበድራሉ»። ወይም ደግሞ ሽማግሌው ማንንም አይጎዳም በሚል አሳብ ከገንዘቡ የተወሰነውን ለራሱ ይጠቀማል። ወይም መሪዎች ስልታዊ ጠቀሜታ ባላቸው ነገሮች ላይ ሳይሆን፣ በምግብና በመጠጥ ወይም በውድ የሙዚቃ መሣሪያዎች ላይ ያውላሉ። በእነርሱ አስተሳሰብ ገንዘቡ የትም ይዋል የት ለውጥ የለውም። እነዚህ ሰዎች ገንዘቡን ባይሰርቁትም፣ አባክነውታል። ስለዚህ መሪዎች ገንዘቡን እንደ ፈለግን ልንጠቀም እንደማንችል መረዳት አለባቸው። ወይም ደግሞ ምእመናን በፈለጉት መንገድ ሊጠቀሙበት አይችሉም። ነገር ግን ገንዘቡ የእግዚአብሔር ስለሆነ፣ እርሱ ለሚፈልጋቸው ሥራዎች መዋል አለበት።

## 3. ገንዘቡ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ጥቅም በሚያስገኙ ነገሮች ላይ መዋል አለበት።



15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በማኅበረሰባችሁ ወይም በዓለም ዙሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሚያደርግ መንገድ ከግልጋሎት ላይ ሊውል የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ከቤተ ክርስቲያናችሁ ገንዘብ ምን ያህል ለአስፈላጊ ነገሮች እየዋለ ይመስልሃል? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለወንጌሉ እጅግ ስልታዊ ባልሆኑ ነገሮች ገንዘቡን እያባከኑ ያሉት እንዴት ነው? መ) በእነዚህ አምብዛም አስፈላጊ ባልሆኑት ነገሮች ላይ የሚውለው የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ምን ያህል ይመስልሃል?

አንድ ሰው ምግብ እንደ መግዛት ወይም ለትምህርት ቤት እንደ መክፈል፣ ገንዘቡን ሁሉ ከረሜላ በመግዛት ሊጨርስ አየኸው እንበል። በዚህ ጊዜ «ምን ዓይነት ብክነት ነው!» ማለትህ አይቀርም። ገንዘብ በጥበብ መጠቀም ያለብን ውድ ሀብት መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ምግብ፣ የቤት ኪራይ መክፈያ ወይም የሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች መሸፈኛ እስከማይኖረን ድረስ ያገኘነውን ገንዘብ ካባከንን፣ ለችግር መጋለጣችን የማይቀር ነው። በዚህ ጊዜ ልንታመም፣ የምናድርበትን ቤት ልናጣና በሕይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሳናገኝ ልንቀር እንችላለን።

በተመሳሳይ መንገድ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለእግዚአብሔር መንግሥት እርባና በሌላቸው ነገሮች ላይ ሊበትኑ ይችላሉ። በማቴዎስ 25:14-30 ከአስተዳዳሪዎቹ አንዱ መክሊቱን አትራፊ ባልሆነ መንገድ ቀብሮ በማቆየቱ ምክንያት ባለቤቱ ምን ያህል እንደ ተናደደ ትመለከታለህ። አስተዳዳሪው በመክሊቱ ምንም ጥቅም የሌለው ነገር ገዝቶ ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ንዴቱ ይጨምር እንደ ነበረ አስብ። ገንዘቡን በመጠቀም ለባሪያዎች ፓርቲ አዘጋጅቻለሁ ቢልስ ኖሮ? ይህን ቢል ኖሮ፣ ባለቤቱ በጣም ተናድዶ አስተዳዳሪውን ከዚህ በበለጠ ይቀጣው ነበር ብዬ አምናለሁ። በዚህ ጊዜ ባለቤቱ ትርፍ ብቻ ሳይሆን ዋናውንም ጭምር አጥቷልና።

አንድ ባለ አደራ የሚቀጠረው የባለቤቱን ሀብት በመጠቀም ተጨማሪ ትርፍ እንዲያመጣ ነው። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ባለቤት ከሆነና፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ ታማኝ ባለ አደራዎች ከሆኑ፣ ገንዘቡን በማብዛት

ለእግዚአብሔር መንግሥት ምርጥ የሆኑትን ነገሮች እንዲያከናውን ማድረግ አለብን። መሪዎች በቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አጠቃቀም ላይ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ፣ «ይህንን ገንዘብ የምንጠቀመው ለእግዚአብሔር መንግሥት ታላቅ ለውጥ ለሚያመጣ ተግባር ነው?» የሚል ጥያቄ ማንሣት አለባቸው። የመዘምራን ልብስ ለመግዛት፣ የሙዚቃ መሣሪያ ለመግዛት፣ ወይም የተሻለ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለመገንባት ገንዘቡን ስለ መጠቀም በምንነጋገርበት ጊዜ፣ «መንግሥቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ መልካም የእግዚአብሔር ገንዘብ ባለ አደራዎች ሆነን እየሠራን ነው? ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚበጀው ገንዘቡን በዚህ መንገድ መጠቀሙ ነው ወይስ ወንጌላዊ መቅጠር ወይስ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያስፈልጉትን መጻሕፍት መግዛት?» ብለን መጠየቅ አለብን።

4. በገንዘብ አጠቃቀሙ ላይ ታማኝነትና ግልጽነት እንዲኖር፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የገንዘብ አስተዳደር የሚመራ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት አለባት።

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የተሰጠውን ገንዘብ ምን አደረገው? ለ) በጉዞው መጨረሻ ላይ ገንዘቡን ምን አደረገው? ሐ) ዕዝራ ይህንን ያደረገው ለምን ይመስልሃል? መ) መሪዎች ጥንቃቄ የተሞላበትና ግልጽነት ያለው የገንዘብ አያያዝ መከተል እንደሚያስፈልጋቸው ይህ የዕዝራ ምሳሌነት ምን ያስተምረናል? |

እግዚአብሔር ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ ጠራው። በኢየሩሳሌም ዕዝራን በመጠቀም እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማነቃቃት ፈልጎ ነበር። ዕዝራ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት የፋርስ ንጉሥ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያስቀምጠውን ገንዘብና ሀብት ሰጠው። ዕዝራ ይህንን ገንዘብ ንጉሡና አይሁዶች በሚረዱበት መንገድ በታማኝነት ካልያዘ፣ ዝናው እንደሚጠፋ ተረድቶ ነበር። ይህ ከሆነ ደግሞ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማነቃቃት አይጠቀምበትም ማለት ነው። ስለዚህ መንገዱን ከመጀመሩ በፊት ዕዝራ ገንዘቡን ቆጥሮ ሰዎች እንዲይዙ ሰጣቸው። ሰዎች ታማኝነቱን እንዳይጠራጠሩ ስለ ፈለገ፣ ገንዘቡን ራሱ ዘንድ



ለማኖር አልፈለገም። ኢየሩሳሌም ሲደርስ ደግሞ ምንም እንዳልጎደለ ለማረጋገጥ ገንዘቡን እንደገና ቆጠረ። በተመሳሳይ መንገድ፣ ዛሬም መሪዎች ታማኝነታቸው ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ ግልጽነት ያለው የሂሳብ አያያዝ መከተል አለባቸው። መሪዎች ሊረዱ የሚገባቸው አንዳንድ እውነታዎች ከዚህ በታች ተመልክተዋል:-

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በአንድ ግለሰብ እጅ ውስጥ እንዳይቀመጥ የሚያደርግ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መከተል አለባት። ይህ ግለሰቡ ገንዘቡን ለመጠቀም እንዳይፈተን ያደርገዋል። ሰይጣን አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች ስለሚያምኗቸው ገንዘቡን በሚያስቀምጡበትም ሆነ በሚቆጥሩበት ጊዜ ሰው ከአጠገባቸው አለመኖሩ ምንም አይደለም ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ወይም ደግሞ የገንዘብ ፈተናን ለመቋቋም የምንችል ጠንካራ ሰዎች ነን ብለን እንድናስብ ያደርገናል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብን አላግባብ ይጠቀማሉ። ይህ ደግሞ የራሳቸውንና የሌሎች አገልጋዮችንም ስም የሚያጠፋ አደገኛ ነገር ነው። ስለዚህ፣ ለራሳቸው መንፈሳዊ ሕይወትና ዝና በማሰብ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብን አላግባብ የመጠቀም ዕድል የሚቀንስ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መከተል አለባቸው። እንዲያውም፣ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አያያዙን የሚቆጣጠር ሥርዓት ከሌላት፣ አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ገንዘቡን በታማኝነት እንደሚይዝ ምእመናን የሚረዱበትን አሠራር በፍጥነት ይዘረጋል።

ለብቻችንና ከሰው ጋር በምንሆንበት ጊዜ የፈተናው ኃይል ምን ያህል እንደሚለያይ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ለምሳሌ ያህል፣ በሆቴል ውስጥ ብቻችንን ሆነን የወሲብ ፈተና ቢገጥመን፣ ፈተናውን መቋቋም ሊከብደን ይችላል። ነገር ግን ከእኛ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ካለው መንፈሳዊ ሰው ጋር አብረን ከሆንን፣ በኃጢአቱ ሳንሸነፍ እንችላለን። የሌላው ሰው መኖር ለፈተና የ«አይሆንም» ምላሽ እንድንሰጥ ይረዳናል። በገንዘብ አያያዝ ላይም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። ገንዘቡ በእጃችን ላይ ካለና ብቻችንን

ከሆንን፣ ከገንዘቡ «የመበደር» ፈተናው ያይሳል። አንድ ቀን መልሼ እተካዋለሁ ብንልም፣ ሳይሳካልን ይቀራል። ሁልጊዜም ገንዘቡን እንዳንመልስ የሚያደርጉን ማመኻኛዎች አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ገንዘቡን ሰርቀነዋል ማለት ነው። እስኪታወቅብንና ዝናችን እስኪጠፋ ድረስ ሰይጣን ምንም ጥፋት እንዳልፈጸምን ይነግረናል። በአጠገባችን ሌላ ሰው ቢኖር ግን፣ ገንዘቡን «የመበደር» ፈተናችን ይቀንሳል።

ስለሆነም ገንዘብን በምንይዝበት ጊዜ፣ ቢያንስ ሁለት ሰዎች መሆን እንዳለብን ማስታወሱ ተገቢ ነው። መባ በምንሰበስብበት ጊዜ ወይም ገንዘቡን ከባንክ (ወይም ከሣጥን) በምናወጣበት ጊዜ፣ ብቻችንን መሆን የለብንም። እንዲሁም አንድ መሪ ለአንድ አማኝ ገንዘብ በሚሰጥበት ጊዜ (ለምሳሌ፣ ዕቃ እንዲገዛ)፣ በኋላ ዝርዝር ሪፖርት እንደሚጠይቀው ማወቅ አለበት። ስለዚህ ለገዛቸው ዕቃዎች ደረሰኝ መያዝ አለበት። ይህ ገንዘቡን አላግባብ የመጠቀም ዕድሉን ይቀንሳል። ለአንድ መሪ፣ «ይህ ወንድም ትክክለኛውን ነገር እንደሚያደርግ አምናለሁ» ማለቱ ትክክል አይሆንም። ለገንዘብ አያያዛችን ግድየለሽ ከሆንንና ግለሰቡ ቢፈተን፣ ክርስቲያናዊ ፍቅር አሳሳየነውም ማለት ነው። በኃጢአት ወድቆ ገንዘቡን አላግባብ ቢጠቀም፣ በከፊል ተጠያቂ መሆን ያለበት መሪው ነው።

የሚያሳስበን ገንዘብን አሳግባብ በመጠቀም አንድ ሰው በኃጢአት መውደቁ ብቻ አይደለም። ስማችንን ለማስጠበቅም እንፈልጋለን። በመሆኑም፣ አንድ ሰው ብቻውን ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ከሆነ፣ ሌሎች ሰዎች በአግባቡ እያንቀሳቀሰ ነው የሚል እምነት ላይኖራቸው ይችላል።

ለ. በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ገንዘቡንና የሂሳብ ደብተሩን በማጤን የተለያዩ መረጃዎች የሚያገኙበት የተጠያቂነት መዋቅር መኖር አለበት።

1) መኖር ያለበት ገንዘብ መኖሩን ማረጋገጥ። በቤተ ክርስቲያን ቢሮ ውስጥ ያለውን የሂሳብ ደብተር መመልከቱ ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህም በላይ የሂሳብ ደብተሩ በባንክ ቤት ውስጥ



እንዳለ የሚያሳየው የገንዘብ መጠን ባንክ ቤት ውስጥ በትክክል መሩን ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው። ይህ አንድ ሰው ገንዘቡን ከባንክ ቤት «መበደር» አለመበደሩን ያሳያል።

2) በአገልግሎት ላይ እየዋለ ያለው ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን አንጂ ለግል ጥቅም አለመዋሉን ማረጋገጥ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ትልቅ ከሆነች፣ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ «ኦዲት» ማድረጉ ጠቃሚ ነው። የሂሳብ አያያዙ ውስብስብ ከሆነ፣ ሙያዊ ብቃት ያለው ኦዲተር መጠቀሙ ተገቢ ይሆናል። ነገር ግን የሂሳብ አያያዙ ያን ያህል ካልተወሳሰበ፣ ጥሩ የሂሳብ እውቀት ያለው መምህር ኦዲት እንዲያደርግ መጠየቅ ይቻላል። ይህ ሰው ገንዘቡን ከሚያዙት ሰዎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው መሆን አለበት። ከቤተ ክርስቲያን የሂሳብ አያያዝ ጋር ቀረቤታ ያለው ሰው ኦዲት ቢያደርግ፣ ሰዎች የተፈጠሩትን ችግሮች ለመሸፋፈን እየሞከረ ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ነገር ግን ግለሰቡ ከሂሳብ አያያዙ ጋር ግንኙነት እንደሌለው ሁሉም ሰው ካወቀ፣ በትክክለኛነቱ ላይ አመኔታ ይኖራቸዋል።

3) ገንዘቡ ሽማግሌዎች ሳጸደቁአቸው ነገሮች እየዋለ መሆኑን ማረጋገጥ። የቤተ ክርስቲያን መሪው የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ እንደ ፈለገ የመጠቀም መብት የለውም። መሪው ለሽማግሌዎች ጉባኤ ሪፖርት ስለሚያደርግ፣ ጉባኤው ካጸደቃቸው ነገሮች ውጭ መጠቀም አይችልም። ገንዘቡን ሽማግሌዎቹ ላላጸደቁት ጉዳይ መጠቀም ቢፈልግ፣ የእነርሱን ፈቃድ ማግኘት አለበት። ሽማግሌዎችም ቢሆኑ ገንዘቡ እነርሱ ሳጸደቁአቸው ነገሮች መዋሉን ማረጋገጥ አለባቸው። ይህ ካልሆነ፣ ሽማግሌዎቹ ጥብቅ የገንዘብ ቁጥጥር በማድረግ የቤተ ክርስቲያን መሪው መቼ ገንዘቡን ሊያወጣ እንደሚችልና መቼ ደግሞ ከሽማግሌዎቹ ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት አለባቸው።

(ማስታወሻ፡- አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ የቤተ ክርስቲያን ሂሳብ እንዳይመረመር ከመከላከል ይልቅ፣ የሂሳብ ምርመራ እንዲካሄድ ግፊት ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ ይህንን የሂሳብ ምርመራ በመጠቀም ታማኝነቱን ሊያረጋግጥለት ይችላል። ይህ

የሚደብቀው ነገር እንደሌለውም የሚያሳይ ነው:: መንፈሳዊ መሪ ታማኝነቱን ለማሳየት ይፈልጋል:: ስሙን ለመጠበቅ ይፈልጋል:: መልካም ስም ለመያዝ ምርጥ የሆነው መንገድ በገንዘብ አያያዝ በኩል ግልጽነትን ማሳፈን ነው::)

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ገንዘቧን ለመንከባከብ የምትጠቀምበትን የሂሳብ አያያዝ ዘዴ አብራራ:: ለ) የገንዘብን አላግባብ መጠቀም በይበልጥ ለመቀነስና ምእመናን በመሪዎቻቸው ላይ የበለጠ እንዲተማመኑ ለማስቻል ምን ዓይነት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ቢመሠረት ይበጃል ትላለህ? |

5. ገንዘቡ ሁልጊዜም ሰዎቹ ለሰጡበት ዓላማ መዋል አለበት:: በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት፣ ገንዘብ ለብዙ ዓላማዎች ይሰጣል:: በመደበኛነት የሚሰጡ የመባና የአስራት ስጦታዎች አሉ:: እነዚህ የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀጣይነት ያላቸው ወጪዎች ለመሸፈንና የወንጌላውያንን ደመወዝ ለመክፈል የሚያስችሉ ናቸው:: (የውኃና የመብራት ሂሳብ ለመክፈል፣ ሕንጻዎችን ለመጠገን፣ ደመወዝ ለመክፈል ያገለግላል::) ብዙውን ጊዜ ግን ለሆነ ዓላማ ገንዘብ የሚሰጥበት ሁኔታም አለ:: ይህም የመዘምራን ልብስ፣ የሙዚቃ መሣሪያ ለመግዛት ወይም ለወንጌል አገልግሎት ሊሆን ይችላል:: ገንዘቡን በሙሉ በአንድ የባንክ ደብተር ወይም በቤት ውስጥ በአንድ ሣጥን ውስጥ የምናኖር ከሆነ፣ ለአንድ ዓላማ የታሰበው ገንዘብ ከአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ጋር ሊቀላቀል ይችላል:: በዚህ ጊዜ አውቀንም ሆነ ሳናውቅ፣ ለወንጌል ስርጭት የታሰበውን ገንዘብ እንሥተን ለመዘምራን ልብስ መግዣ ልንጠቀምበት እንችላለን:: ይህን በማድረጋችን ለምእመናን ውሸትን ተናግረናል:: ምክንያቱም ገንዘቡን እናውላለን ላልነው ተግባር አላዋልነውም:: ስለሆነም፣ ገንዘቡን ለታለመለት ዓላማ ለማዋል የሚቻልበት የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱ አስፈላጊ ነው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአንድ የሂሳብ ደብተር ገንዘብ «ተበድሮ» ሌላኛውን ችግር ለመፍታት በሚሞክሩበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘቡ ለቤተ



ክርስቲያን እስከ ተሰጠ ድረስ ለፈለግነው ዓላማ ልናውለው እንችላለን የሚል አሳብ ሊኖራቸው አይገባም:: <u>በመጀመሪያ</u>፣ ያለ ሰጪው ፈቃድ ለአንድ ዓላማ የታሰበውን ገንዘብ ለሌላ መጠቀም የግለሰቡን አመኔታ የሚያሳጣ ነገር ነው:: አንድ ሰው ገንዘብ ሊሰጥና እኛም እንደ ቤተ ክርስቲያን ስንቀበል፣ በተስማማንበት መንገድ ለመጠቀም ቃል ገብተናል ማለት ነው:: ይህ ካልሆነ፣ ለግለሰቡ የሰጠነው ቃል ዋጋ የለውም ማለት ነው:: ገንዘቡን ወስዶ ለሌላ አገልግሎት መጠቀም (አገልግሎቱ ጥሩ ሥራ ቢሆንም)፣ ለግለሰቡ የገባነውን ቃል ሳላልፈጸምን ዋሽተናል ማለት ነው:: ግለሰቡ ገንዘቡን ለወንጌል ስርጭት ሰጥቶ ሳለ እኛ ግን ለሕንጻ ጥገና ብንጠቀምበት፣ ሰጪው እውነቱን ባወቀ ጊዜ እንደ ተታለለ በማሰብ ለወደፊቱ ለወንጌል መስጠቱን አይቀጥልም:: ገንዘቡን ለሌላ ነገር ለመጠቀም ብንፈልግ እንኳን፣ ለአንድ ዓላማ የተሰጠውን ገንዘበ ለሌላ ነገር ከመጠቀም መቆጠብ አለብን:: ወይም ደግሞ ገንዘቡን የሰጡት ሰዎች ለሌላ ዓላማ እንድንጠቀምበት እንዲፈቅዱልን ማድረግ አለብን::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ለአንድ ዓላማ (ለምሳሌ፣ ለወንጌል) የታሰበውን ገንዘብ ለሌላ ሥራ (ለምሳሌ፣ ኮንፍረንስ ለማዘጋጀት) መጠቀሙ ችግሮችን ወደ መፍጠሩ ያዘነብላል:: ብዙውን ጊዜ ገንዘቡን መልሰን ሳንተካ እንረሳለን:: ይህ ደግሞ ከሌላው አገልግሎት ላይ ገንዘቡን እንድንሰርቅ ያደርገናል:: ወይም ደግሞ ገንዘቡ የተሰጠው አገልግሎት የገንዘብ እጥረት ስለሚኖርበት፣ ሥራው ይስተጓጎላል:: መሪዎች የወንጌላውያንን ደመወዝ እንሥተው አጣዳፊ ነው ላሉት ችግር የሚያውሉበት ጊዜ አለ:: ከዚያ በኋላ ገንዘቡን በፍጥነት ማግኘት ስለማይቻል፣ ወንጌላውያን ደመወዛቸውን ሳያገኙ ይቀራሉ:: በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለብዙ ወራት የወንጌላውያን ደመወዝ የሚዘገይባቸው ሁኔታዎች አሉ:: ይህ ቤተ ክርስቲያን ሠራተኞቿን እንድትበድል የሚያደርግ ነገር ነው:: ቤተ ክርስቲያን ስትቀጥራቸው በየወሩ ደመወዛቸውን ለመክፈል ተስማምታለች:: ገንዘቡን ወስደን ለሌላ ነገር በመጠቀማችን የገባነውን ቃል አለመጠበቁ፣ የእነርሱ የሆነውን ነገር እንደ መስረቅ ነው:: ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሚሠራበት ድርጅት በየወሩ

ደመወዝ ሳይከፈለው በደስታ ሊሠራ እይችልም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከዓለማዊ ሥራቸው ደመወዝ እያገኙ፣ ወንጌላውያን ያለ ደመወዝ እንዲያገለግሉ የሚጠብቁት እንዴት ነው? ይህ ትክክል ነው? ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጥስ ነገር ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ለሠራተኛ በፍጥነት ደመወዙ ሊከፈለው እንደሚገባ ያዝዘናል:: (ዘዳግ. 24:14-15፤ ኤር. 22:13፤ ያዕ. 5:4 አንብብ::)

ገንዘብ ከለጋሽ የሚመጣ ከሆነና ኦዲት ተደርጎ ጉድለት ከታየ፣ ለጋሹ ገንዘቡ እንደ ተሰረቀ ያስባል:: ይህ ደግሞ ስማችንን ያጠፋዋል:: እንዳንድ እብያተ ክርስቲያናት ከለጋሾች የተቀበሉትን ገንዘብ ለታለመው ፕሮጀክት ላይሆን፣ ለራሳቸው የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች በመጠቀማቸው፣ ለጋሾች ገንዘብ መስጠታቸውን ያቆሙባቸው ሁኔታዎች እሉ::

(ማስታወሻ:- ለጋሹ ለመስማት የሚፈልገውን እሳብ በመናገር ገንዘቡን የምንፈልግበትን ትክክለኛ ምክንያት መደበቁም ስሕተት ነው:: ይህ የውሸት እንደኛው መገለጫ ነው:: እንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለጋሹ ለዚህ ዓላማ ገንዘብ አይሰጠኝም ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ መጠየቅ የለበትም:: ለጊዜው ለጋሹ ላላመነበት ዓላማ ገንዘብ እንዲሰጥ ልናታልለው እንችላለን:: እንድ ቀን ግን እውነቱ ይታወቅና ለጋሹ ቤተ ክርስቲያኒቱ በደል እንዳደረሰችበት ያስባል:: የቤተ ክርስቲያን መሪውን እንደ ውሸተኛ ይቆጥረዋል:: ከዚያ በኋላ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እገልግሎቶች ገንዘብ መስጠቱን ያቆማል:: እግዚአብሔር ለሥራው የሚያስፈልገውን ገንዘብ እንደሚሰጠን ካመንን፣ ገንዘቡን የምንፈልግበትን ምክንያት በግልጽ ለለጋሹ መናገር አለብን:: እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ፣ ለጋሹ ወይም ሌላ ሰው ለሥራው ገንዘብ እንዲሰጥ ያደርጋል:: ገንዘቡ ካልተገኘ፣ ለጊዜው እግዚአብሔር ሥራውን እንድናከናውን እለመፈለጉን ልንረዳ እንችለለን:: ሰዎችን በማታለል በሥጋ የምንሠራው ነገር የእግዚአብሔር በረከት አይኖረውም:: ይህ የራሳችንን መንግሥት - የግል ወይም የቤተ ክርስቲያን ዝና ለመገንባት እየጣርን መሆናችንን የሚያሳይ ነው::)



18ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአንድ ሥራ የታሰበውን ገንዘብ ለሌላ ሲጠቀሙ የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ይህ ችግር በቤተ ክርስቲያን እንዴት ችግሮችን እንዳስከተለ አብራራ::

6. ገንዘቡ በሥራ ላይ ስለ ዋለበት ሁኔታ ለለጋሾችና ምእመናን በየጊዜው ሪፖርት መደረግ አለበት:: እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ተ ጠያቂ ከምንሆንባቸው መንገዶች እንዱ ለምእመናን ገንዘባቸው እንዴት እገልግሎት እየሰጠ እንዳለ መናገር ነው:: ለምእመናን በገንዘባቸው ምን እያደረግን እንደ ሆነ ካልተናገርን፣ ገንዘቡን በታማኝነት እየተጠቀምን አይደለም ማለት ነው:: በየሦስት ወሩ ወይም ቢበዛ በየስድስት ወሩ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን በመባና በሌሎችም መንገዶች የሰጡት ገንዘብ እንዴት ቤተ ክርስቲያኒቱን እያሰገለ እንዳለ ማሳወቅ አለባቸው:: ሪፖርቱ የማይቀርብላቸው ከሆነ፣ ምእመናን ገንዘቡ በታማኝነት ለእገልግሎት መዋሉን በተመለከተ ጥርጣሬ ውስጥ ይገባሉ:: ነገር ግን መሪዎች በግልጽ የሂሳብ መረጃውን የሚሰጡ ከሆነ፣ ምእመናን በበለጠ ያምኗቸዋል::

እንዳንድ እብያተ ክርስቲያናት በሚከተሉት መንገዶች የሂሳብ ሪፖርቶችን ማስተናገድ ውጤታማ ነው ብለው ያምናሉ:-

ሀ. ከዋና ዋና የእገልግሎት ዘርፎች (ለምሳሌ፣ ወንጌላዊ፣ መጋቢ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ዳይሬክተር፣ የልማት ሥራ አስተባባሪ፣ ወዘተ. . .) ሪፖርቱ በቀረበበት የጊዜ ክልል ውስጥ እግዚአብሔር ስላከናወናቸው ነገሮች ምስክርነቶችን እንዲሰጡ ማድ ረግ:: ሰዎች ከሪፖርቶች ይልቅ ምስክርነቶችን ሲሰሙ ደስ ይላቸዋል:: እግዚአብሔር ገንዘባቸውን በመጠቀም እንዴት የሰ ዎችን ሕይወት እየለወጠ እንዳለ በሚረዱበት ጊዜ የበለጠ ለመስጠት ይነሣሣሉ:: እነዚህ አገልጋዮች በገንዘብ እጥረት ምክንያት ሊሳኩ ያልቻሉትን ሕልሞቻቸውንም ሊገልጹ ይችላሉ::

ለ. ባለፈው ዓመት እግዚአብሔር ስላሳየው ታማኝነት የምስጋና በዓል ማዘጋጀት:: እንዳንድ መሪዎች ሪፖርት ለማቅረብ ብቻ ስብሰባ ከማካሄድ ይልቅ፣ በየዓመቱ መጨረሻ ላይ በዓል ያዘጋጃሉ:: በመዝሙሮችና በሪፖርቶች እማካኝነት እግዚአብሔር

ቤተ ክርስቲያን ለመሆን ሲሆን ይችላል:: ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር መፎካከሩ ጤናማ ስላልሆነ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: የክብር ፍላጎታችን በአሁኑ ሰዓት እግዚአብሔር የማይፈልገውን ነገር ለማድረግ ያለንን ገንዘብ እንድንጠቀም ሲያደርገን እንደሚችል መታሰብ አለበት::)

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔርና ሕዝቡ የሚያስፈልገንን ገንዘብ እንደሚሰጡን ብቻ ሳይሆን፣ ገንዘቡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንደሚገኝ ማወቅ አለብን:: መጀመሪያ እግዚአብሔር ገንዘቡን እንዲሰጠን በማንጠብቅበት ጊዜ ገንዘብ እናባክናለን:: ለምሳሌ፣ ለሲሚንቶ መግዣ ገንዘብ ሳይኖረን ኮንትራክተር ብንቀጥር፣ ለእርሱ የምንከፍለው ገንዘብ ይባክናል ማለት ነው:: ወይም ደግሞ ለቆርቆሮ መግገ ገንዘብ ሳይኖረን አጠናዎችን እንገዛለን:: ገንዘቡን አግኝተን ቆርቆሮ ስንገዛ ደግሞ፣ ቀደም ሲል የተገዙት አጣናዎች በምስጥ ተበልተው ከጥቅም ውጪ ሲሆኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔር የሰጠንን ጥበብ ሳንጠቀም ቀርተን ገንዘብ ብናባክን፣ ይህ የእግዚአብሔር ጥፋት አይደለም::

ስለዚህ ማንኛውንም ትልቅ ሥራ ከመጀመራችን በፊት፣ በአስፈላጊው ሰዓት ለሥራው የሚያስፈልገውን ገንዘብ እንደምናገኝ በእምነት እርግጠኞች መሆን አለብን:: ጳውሎስ ከፍቅር በቀር የማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ብሎናል (ሮሜ 13:8):: ቤተ ክርስቲያን ፕሮጀክቶቿን ለማካሄድ ገንዘብ መበደር የለባትም - ዕዳዋን ለመክፈል የሚያስችል ገንዘብ በቅርቡ እንደምታገኝ እርግጠኛ እስካልሆነች ድረስ::

20ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን ካላት ገንዘብ በላይ እንድታከናውን የሚጠይቅበትን ሁኔታ ግለጽ:: ይህንን የሚያደርገው ለምንድን ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያን ከምትችለው ያለፈ ነገር ለማከናወን ሞክራ በራሷና በእግዚአብሔር ላይ ኀፍረት ያመጣችበትን ሁኔታ አይተህ ከሆነ አብራራ:: ሐ) ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በእምነት እንድታከናውን በሚጠይቃቸውና ራሳቸው ከአቅማቸው በላይ ለማከናወን በሚፈልጓቸው ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት ልታውቅ ትችላለች?



9. አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማኅበረ ምእመናቸው የሚጠብቀውን የገንዘብ አያያዝ ሁኔታ ማወቅ አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን አስተዋይነት ነው ብለው በሚያስቡት መንገድ ገንዘብ የማይዙ ከሆነ፣ ብዙም ሳይቆይ ምእመናን በመሪዎቹ ላይ የነበራቸውን እምነት ያጣሉ:: በገጠርና በከተማ፣ እንዲሁም ብዙዎች አባላት ነጋዴዎች በሆኑባቸውና የቀን ሠራተኞች በሆኑባቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የተለያየ የገንዘብ አያያዝ ሁኔታዎች ይኖራሉ:: የሚከተሉት ምእመናን ስለ ገንዘብ አያያዝ ከሚያስቧቸው ነገሮች አንዳንዶቹ ናቸው:-

ሀ. አነስተኛ አብያተ ክርስቲያናት፣ በተለይም በገጠር ያሉ ወይም አነስተኛ ገቢ ያላቸው አባላት የሚገኙባቸው የከተማ አብያተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በሚገባ ይያዛል ብለው ስለሚያስቡ፣ ገንዘቡ ይባክናል የሚል ግምት አይኖራቸውም:: ምእመናን ጥሩ ምግብ የማግኘት ችግር ካለባቸው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ምግብ ሲመገቡ ሲያዩ ደስ አይላቸውም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በጥንቃቄ እንዲይዙ ይፈልጋሉ:: አነስተኛ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በገንዘቡ አወጣጥ ላይም ጥብቅ አቋም አላቸው:: አገልግሎቶች ቀደም ሲል በነበረው መንገድ እንዲካሄዱ ይፈልጋሉ:: ለምሳሌ፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዳለው፣ «ከዚህ በፊት ለወንጌላዊ ከ150 ብር በላይ ከፍዬ አላውቅም:: አሁንም ቢሆን ከዚህ በላይ ልከፍል አልችልም» ብሏል:: ይህንን የተናገረበት አንዱ ምክንያት ቀደም ሲል የነበረውን ሁኔታ ከአሁኑ ጋር ለማገናዘብ ባለመቻሉ ነው:: በአነስተኛ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ መሪዎችና አገልጋዮች ይህንን የገንዘብ አመለካከት ማወቅ አለባቸው:: ምእመናን እንደ ብክነት እንዳይቆጥሩባቸው፣ የገንዘብ አወጣጡ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው::

ለ. በከተማ አካባቢ የሚኖሩ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ገንዘብ በፍጥነት በማሰባሰብና ለአዳዲስ ነገሮች በመጠቀም ላይ ያተኩራሉ:: ቤተ ክርስቲያን በእድሜ እየገፋች በሄደች መጠን፣ ምእመናን አዳዲስ ነገሮችን ለመጀመር ወይም ለአዳዲስ ነገሮች

ገንዘብ ለማስባሰብ ፈቃደኛ መሆናቸው ይቀንሳል:: በአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ሰዎች አስቸጋሪ ነገሮችን በእምነት በማከናወኑ ላይ ያተኩራሉ:: ከትንሽ ይልቅ ጥራት ያለው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ለመገንባት እግዚአብሔር ይረዳናል ብለው ያምናሉ:: በተለይ ከፍተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸው የተማሩ አባላት ያሉባቸው አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት፣ አስፈላጊ ናቸው ለሚሏቸው አዳዲስ ሥራዎች ገንዘባቸውን ያውላሉ:: ለምሳሌ፣ ለምእመናን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ማካሄድ አስፈላጊ ነው ብለው ቢያስቡ፣ በፍጥነት ገንዘብ መድበው መጻሕፍት ይገዛሉ፣ ወዘተ. . . :: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ይህንን አዳዲስ ነገሮችን የመሞከር ፍላጎት በመረዳት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዳዲስ ነገሮችን ማካሄድ አለባቸው:: ችግሩ እንዲህ ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት ለውጫዊ ታይታ ብዙ ነገሮችንና ገንዘቦችን ያባክናሉ:: (ከእነዚህ ውጫዊ ነገሮች መካከል የታወቀ የመዘምራን ቡድን መመሥረት፣ ትልቅ ሕንጻ መገንባት፣ ወይም ምርጥ የድምጽ ሲስተም መግዛት ይገኙባቸዋል::) እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለተመልካች አስደናቂ ስለማይመስሉ፣ መንፈሳዊ እድገትን በሚያመጡ ነገሮች ላይ ገንዘባቸውን ለማውጣት እምብዛም ፈቃደኞች አይሆኑም::

ሐ. በተለይ ብዙ የተማሩ ሰዎች ያሉባቸው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በገንዘብ አወጣጥ ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ይፈልጋሉ:: እምብዛም የተማሩ አባላት የማይገኙባቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመሰላቸው መንገድ ውሳኔዎችን ሁሉ እንዲሰጡ ይፈልጋሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ልዩነቶች መረዳት አለባቸው:: በመጀመሪያው ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ መሪዎች ምእመናን በገንዘብ አወጣጥ ላይ ምክር እንዲሰጧቸው መፍቀድና ገንዘቡን የተጠቀሙበትን መንገድ በግልጽ ማሳየት አለባቸው:: መሪ ዎች ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች ከምእመናን በሚቀርቡላቸው ጊዜ፣ እንደ ጥርጣሬ ወይም አመራራቸውን እንደ መፈታተን አድርገው መቁጠር የለባቸውም:: ይህ ምእመናን የገንዘብ አያያዙን ጨምሮ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ለመሳተፍ መፈለጋቸውን



የሚያሳይ ምልክት መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል:: ነገር ግን አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በሁለተኛው ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግል ከሆነ፣ ምእመናን ስለ ገንዘብ አወጣጡ አሳብ እንዲሰጡት በሚጠይቅበት ጊዜ፣ ዝም ማለታቸው የማይቀር ነው:: ለዚህም ምክንያቱ መሪው ሁሉንም ዓይነት ውሳኔ ዎች እንዲሰጥ የሚጠብቁ መሆናቸው ነው::

መ. በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ አባላት የሚገኙባቸው ትላልቅ የከተማ አብያተ ክርስቲያናት ገንዘቡ የመሪዎቹን ታማኝነት በሚያሳይ ሙያዊ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት እንዲመራ ይፈልጋሉ:: ትክክለኛ ደረሰኞች፣ የኦዲት ሥርዓት፣ ወዘተ. . . እንዲኖር ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ትናንሽ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ዓይነቱን ቁጥጥር የመተማመን አለመኖር ምልክት አድርገው ይመለከታሉ:: ቀላል የገንዘብ አስተዳደር መንገዶች ያስደስቷቸዋል::

ሠ. በሽማግሌ መሪዎች የሚመሩ ትውፊታዊ አብያተ ክርስቲያናት እኛ ብቻ የገንዘብ ጉዳዮችን መወሰን አለብን ባዮች ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ሰዎች እንደ «እምባገነኖች» እና ገንዘቡን በሙሉ ብቻቸውን እንደሚቆጣጠሩ ሰ ዎች አድርገው ይመለከቷቸዋል:: ለትንሽዋ ገንዘብ ሳይቀር አገልጋዮቹ ከእነርሱ ገንዘብ እንዲጠይቁ ይፈልጋሉ:: ወጣት መሪ ዎች አገልጋዮቻቸው የገንዘብና የአገልግሎት ውሳኔዎችን እንዲሰጡ ይፈቅዱላቸዋል:: እነዚህ አዳዲስ መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጊዜያቸውንና ገንዘቡን የተጠቀሙበትን ሁኔታ እንዲያሳውቁ በማድረግ በውክልና ይሠራሉ::

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት በገንዘብ ላይ ያላቸውን አመለካከት ገምግም:: አባላት በገንዘብ ጉዳይ ከላይ ከተመለከቱት መካከል የትኞቹን ይመስላሉ? ለ) በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በምእመናን፣ ወይም በተማሩና ባልተማሩ አባላት መካከል የአመለካከት ልዩነት አለ? አብራራ:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን የሚፈልጉትን የገንዘብ አያያዝ መንገድ ማወቅ ለምን ያስፈልጋቸዋል?

10. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በማስተዋልና በጥንቃቄ እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ያለውን አመለካከት ለምእመናን ማስተ

ማር አለባቸው:: አንደ ሌሎች መንፈሳዊ እውነታዎች ሁሉ፣ ምእመናን ገንዘባቸውን ስለሚጠቀሙበት መንገድ በተደጋጋሚ ማስታወሱ ተገቢ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገንዘብ የሚያስተምረውን እውነት በሚገባ ያውቃሉ ብለው መገመት የለባቸውም:: ይሁን እንጂ፣ ስለ ገንዘብ መናገሩ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነገር ነው:: ጥንቃቄ ካልተደረገበት፣ ምእመናን፣ «አሁንም ተጨማሪ ገንዘብ እንድንሰጣቸው እየወተወቱን ነው:: መሪዎች ለዋናው ጽ/ቤት፣ ለአውራጃ፣ እንዲሁም ለሕንጻ ግንባታ ገንዘብ እንድንሰጣቸው ይፈልጋሉ:: እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉት ገንዘብ ብቻ ነው» ብለው ሊያስቡ ይችላሉ:: እንዲህ ዓይነት አመለካከት በሚኖራቸው ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ብዙም የመስጠት ፍላጎት አይኖራቸውም:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለማከናወን የሚፈልገውን ሥራና ለምእመናን ለመስጠት የሚፈልገውን በረከት ይገድባል:: ቀደም ብለን እንዳጠናነው፣ እግዚአብሔር የሚፈልገው ሌሎችን እንድንባርክ የሚያስችል በረከት በእኛ ውስጥ ለማኖር ነው:: ገንዘቡን ተጠቅመን ሌሎችን ለመባረክ በማንፈልግ ጊዜ፣ እርሱም ለእኛ በልግስና መስጠቱን ያቆማል:: አንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች፣ ስለ መስጠት ማስተማር ያለብን ገንዘብ በሚያስፈልገን ጊዜ ብቻ መሆን የለበትም:: የገንዘብ ችግር በማይኖርበት ጊዜ ጭምር አንደ ሌሎቹ ሁሉ ዓመቱን ሙሉ ከሚሰጡት ትምህርቶች መሐል እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ጉዳዮች እንድናውቅ የሚፈልጋቸው እውነቶችም መካተት አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያስተምሩ ከሚገባቸው ነገሮች ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. በቀዳሚነት አግዚአብሔር የሚፈልገው ሰዎች በሁለንተናዊ ሕይወታቸው ለእርሱ አንዲገዙ ነው:: በዋናነት የሚያሳስበው ገንዘብ መስጠታቸው አይደለም (2ኛ ቆሮ. 8:1-5):: ልጆቹ ሕይወታቸውን ሁሉ ለእርሱ ሲያስገዙና ፈቃዱን ለማድረግ ሲፈልጉ ገንዘባቸውንም ይቀበላል:: ሰዎች በእግዚአብሔር ሥራ ዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ስታደርግ፣ ገንዘባቸውን ለአግዚእብሔር ለመስጠት ፈቃደኞች ይሆናሉ::



ለ. ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው:: እንድንሠራ ከሚያደርጉን ምክንያቶች አንዱ ምንም ለሌላቸው ሰዎች እገዛ ለማድረግ እንድንችል ነው (ኤፌ. 4:28፤ 2ኛ ተሰ. 3:6-15)::

ሐ. እግዚአብሔር ለጋሾች እንድንሆን ይፈልጋል:: የሚያስደስተው አሥራታችን ብቻ አይደለም:: በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ያላትን ትንሽ ነገር የምትሰጠው ድሀ መበለት አሥራት ከሚሰጥ ሀብታም በላይ መሥዋዕትነትን ታደርጋለች (ማር. 12:41-44):: የአስራት መርሕ በገንዘባችን እግዚአብሔርን ማክበራችን ነው:: ከዚህ የሚበልጠው ለእግዚአብሔር በልግስና መስጠታችን ነው:: ልግስና በምንሰጥበት ጊዜ ምን ያህል እንደምንጎዳ የሚያሳይ ነው:: ብዙውን ጊዜ 1000 ብር የሰጠውን ነጋዴ ወደ ማመስገኑ በማዘንበል እንሳሳታለን:: እርሱ ምናልባት ይህንን ገንዘብ በመስጠቱ ምንም ያህል አልተጎዳም ይሆናል:: ነገር ግን ከሚያገኘው አንጻር ብዙ መሥዋዕትነት የጠየቀበትን አሥር ብር የሚሰጠውን የቀን ሠራተኛ ቸል እንለዋለን:: ብዙ ገንዘብ የሚሰጡትን ሰዎች ስም በመጥቀሳችንና በማመስገናችን በአግዚአብሔር ዓይኖች ፊት በበለጠ በልግስና የሚሰጡትን ሰዎች ተስፋ እናስቆርጣለን:: «የሚሰጡት የሌሳቸውን እጆች ባርክ፣» ብለን በመጸለያችን ራሱ ድሆች ለእግዚአብሔር እንዳይሰጡ እናበረታታለን:: እግዚአብሔር ባርኮአቸው በሳምንቱ ውስጥ ምግብ ማግኘት ከቻሉ፣ የተወሰነች ነገር ለእግዚአብሔር በመስጠት ስለ መገባቸው ሊያመሰግኑት ይችላሉ:: ክርስቶስ ድሀይቱ ሴት የሌላትን ነገር እንዳትሰጥ አልተከላከላትም:: ነገር ግን በልግስና ስለ ሰጠች አመሰገናት::

መ. አግዚአብሔር ሕዝቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያገለግሉ ሰዎች እንዲከፍሉ ይጠብቃል (ኢዮብ 31:13-15፤ ቈላ. 4:1):: አንዳንድ ክርስቲያኖች ያለ ገንዘብ ጊዜያቸውን ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ሊያውሉ ቢችሉም፣ ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ለሚያገለግሉ ሰዎች ደመወዝ መከፈል አለበት:: ቀደም ሲል አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት በአራሽ ማኅበረሰቦች ውስጥ በነበሩባቸው ጊዜያት፣ ለወንጌላውያንና መጋቢያን ብዙ ደመወዝ መክፈል ያን ያህል አስፈላጊ አልነበረም:: እንደ ተቀሩት ሰዎች

ሁሉ፣ ከእርሻ በሚያገኙት ሀብት ቤተሰቦቻቸውን ማስተዳደር ይችሉ ነበር። አሁን ግን ብዙ አገልጋዮች ሙሉ ጊዜያቸውን ለቤተ ክርስቲያን ስለሚሰጡ፣ ቤተ ክርስቲያን ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ሚዛናዊ ነው የምትለውን ደመወዝ መመደብና በጊዜው መክፈል ይኖርባታል። «ሚዛናዊ» የሚባለው ነገር የግድ የትምህርት ደረጃን ያገናዘበ ላይሆን ይችላል። ይህ በይበልጥ የሚወሰነው በቤተ ክርስቲያኒቱ የገንዘብ አቅም ነው። አገልጋዮች በቂ ደመወዝ ባለማግኘታቸው የሚቸገሩ ከሆነ፣ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ለአገልግሎቱ ሊሰጡ አይችሉም። በቀጣዩ ወር ለሚያስፈልጋቸው ወጪ ገንዘቡን ከየት እንደሚያመጡት በማሰብ አእምሯቸውንና ጉልበታቸውን ሊያባክኑ ይችላሉ። አስተዋይ ምእመናን አገልጋዮቻቸው ስለሚተዳደሩበት ገንዘብ ሳይጨነቁ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ላይ ሙሉ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ ለማስቻል በቂ ደመወዝ ይከፍሏቸዋል።

ሠ. እግዚአብሔር ከውጫዊ ነገሮች ይልቅ በውስጣዊ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል። ጥሩ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ፣ የድምጽ ማጉያ፣ ኪ-ቦርድ፣ የመዘምራን ልብስ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ከሆነው በላይ እያንዳንዱ ምእመን በመንፈሳዊ ሕይወት መብሰሉና ወንጌሉን ላልዳኑት ሰዎች ማዳረሱ አስፈላጊ ነው። ምእመናን መንፈሳዊ እድገት ከሚያመጡ ነገሮች ይልቅ በውጫዊ ነገሮች ላይ ገንዘባቸውን ማባከን ይፈልጋሉ። ይህ አስተዋይ የገንዘብ አጠቃቀምን የሚያሳይ አይደለም።

ረ. እግዚአብሔር ተስፋ ስላልሰጠው ነገር ተስፋ አለመስጠት። እግዚአብሔር ታማኝነታችንን በማክበር የበለጠ ብዙ ገንዘብ ይሰጠናል። ይህንንም የሚያደርገው የበለጠ ለእርሱ መልሰን እንድንሰጠው ነው። ነገር ግን በሰጠነው ልክ መልሶ እንደሚሰጠን ቃል አይገባልንም። አንዳንድ ሰባኪዎች ለእግዚአብሔር አንድ መቶ ብር ብትሰጥ፣ እግዚአብሔር ሁለት መቶ ብር ይሰጥሃል ይላሉ። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ቃል አልገባልንም። በርግጥ በልግስና የሚሰጡትን ሰዎች እንደሚባርክ ቃል ይገባል። ነገር ግን ያ ቃል ኪዳን ከሞትን በኋላ በመንግሥተ ሰማይ የሚፈጸምልንም ሊሆን



ይችላል። እግዚአብሔር ለእርሱ ስለ ሰጠን የተሻለ ቤት ወይም ሥራ እንደምናገኝ ቃል አይገባልንም። ሰዎች አዲስ ሥራ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ለእግዚአብሔር ገንዘብ ቢሰጡና ምንም ነገር ባያገኙ፣ ወደፊት የመስጠት ፍላጎታቸው ይሞታል። ለእግዚአብሔር በመስጠት የሚያገኙትን ደስታ ያጣሉ። ያጋጠማቸው ችግር መንፈሳዊ ሕይወታቸውን፣ ብሎም በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነትና ፍቅር ይቀንስባቸዋል።

ሰ. ሰዎች ባለመስጠታቸው «የጥፋተኝነት» ስሜት እንዲሰማቸው አታድርግ። ወይም ደግሞ በመስጠት ሊያገኙ በሚችሏቸው ግላዊ ጥቅሞች ላይ እንዲያተኩሩ አታድርግ። ነገር ግን ካለን ገንዘብ ለእግዚአብሔር በመስጠታችን የምናገኘውን ዕድል እንዲገነዘቡ ለማገዝ ሞክር። መስጠት እግዚአብሔር ላደረገልን መልካም ነገር ሁሉ የምንሰጠው የምስጋና ምላሽ መሆኑን አስገንዝባቸው። በመጨረሻም፣ ሰዎች በሁለንተናቸው እግዚአብሔርን እንዲወድዱት አሳስባቸው። ክርስቶስ የሚወደኝ ትእዛዜን ይጠብቃል ብሏል (ዮሐ. 14:21)። ሰዎች እርሱን ብመውደድ እንጂ በመፍራት እንዲታዘዙት አልፈለገም።

ሸ. እግዚአብሔር ሥራውን የሚያከናውነው በእኛ አማካኝነት እንጂ ከሰማይ በረከትን በማውረድ እንዳልሆነ አስገንዝባቸው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» በሚል ማመኻኛ ከመስጠት ይቆጠባሉ። ምእመናን በአመዛኙ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ገንዘብ ከእግዚአብሔር እንደምታገኝ አያስቡም። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ ገንዘብ በሚጠይቃቸው ጊዜ ኀፍረት ይሰማቸዋል። ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ቀጣናዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ወይም ዋናው ጽ/ቤት በሚያደርግላቸው አገልግሎት ደስተኞች ናቸው። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ አገልግሎቶች «ነጻ» እንደ ሆኑና እግዚአብሔር ከሰማይ በሚያዘንበው ገንዘብ የሚንቀሳቀስ ይመስላቸዋል። ይህንን የተሳሳተ ግንዛቤ ማረም አለብን። እግዚአብሔር የሚሰጠው እኛ ስንሰጥ ነው። ለሕዝቡና ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጠው ሕዝቡ ገንዘባቸውን ሊሰጡ ነው። እርሱ የመረጠው ይህንኑ መንገድ ብቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች

ቤተ ክርስቲያን ከተጨባጩ ዓለም የተለየች ነች ብለው ያስባሉ። በሥራ ዓለም ለሠራተኞች ደመወዝ መክፈል አለበት። በቤተ ክርስቲያን ግን እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ ይሰጣቸዋል በሚል አሳብ ደመወዝ ላለመክፈል እንጥራለን። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔ ር ለሠራተኞቹ ለመስጠት የፈለገው በዚህ መንገድ አይደለም። በመባችን እንድንሰጣቸው ነው የሚፈልገው። በቤታችን የስልክ፣ የመብራት፣ የውኃ፣ የቤት ጥገና፣ ወዘተ. . . ወጪዎችን እናወጣለን። እነዚሁ ወጪዎች በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ እንዳሉ ለምእመናን ማስተማር አለብን። በምንሰጠው ገንዘብ የሚደገፉ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ወጪዎች አሉ።

ስለ ገንዘብ ምእመናንን ከማስተማሩ ጎን ለጎን አስፈላጊ የሆነው ሌላው ነገር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በገንዘባቸው ምሳሌነትን ማሳየታቸው ነው። በአመዛኙ ስለ ገንዘብ ብዙ የሚሰብኩ ሰዎች አምብዛም የማይሰጡ ሆነው ይገኛሉ። በአንዳንድ አገሮች መጋቢዎች እጅግ ምስኪን ሰዎች ተደርገው ይወሰዳሉ። በልግስና እንደምንሰጥ ቢያውቁ፣ ሰዎች ስብከታችንን ለመስማት የበለጠ ፈቃደኞች ይሆናሉ። በተጨማሪም፣ እኛ የማንሰጥ ሆነን ሳለ በልግስና ስለ መስጠት መስበክ የግብዝነትን ኃጢአት መፈጸም ነው። ይህ ክርስቶስ እጅግ ከተቃወማቸው ኃጢአቶች አንዱ ነው (ማቴ. 23ን አንብብ)።

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ እግዚአብሔር በገንዘብ ላይ ያለውን አመለካከት ለምእመናን በሚገባ የምታስተምር ይመስልሃልን? መልስህን አብራራ። ለ) በቤተ ክርስቲያን ስለ ገንዘብ ማስተማር የሚያስፈልጉ ሌሎች እውነታዎች ምን ምንድን ናቸው? |

11. ለቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልግ ገንዘብ በምናስተምርበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወሱ ጠቃሚ ይሆናል፡-

ሀ. በተደጋጋሚ ስለ ገንዘብ ችግር አታውራ። አንዳንድ መጋቢ ዎች በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ስለ መስጠት ማስተማር አያስፈልግም ይላሉ። ብዙ ጊዜ የገንዘብ ጥያቄ በሚቀርብላቸው ጊዜ ሰዎች «እንደ ጨቀጨቅናቸው» ዘማሰብ ይናደዳሉ። አንዳንድ ቤተ እምነቶች በተደጋጋሚ የገንዘብ ጥያቄ በማቅረባቸው የምእመኖቻቸውን አክብሮት ያጣሉ።

ለ. ለጎብኚዎቹ ስለ ገንዘብ ጉዳዮች የምትናገረው ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት መሆኑን ንገራቸው። አለበለዚያ ጎብኝዎቹ ሁልጊዜም ገንዘብ የምትጠይቅ ይመስላቸውና እንደገና ላይመጡ ይችላሉ።

ሐ. ልዩ መባ የምትሰበስብ ከሆነ፣ ለምእመናኑ ቀደም ብለህ ግለጽላቸው። ይህ ማስታወቂያ ካልተናገራቸው የሚሰጡትን ነገር ይዘው ላይመጡ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ በስሜታዊነት ተነሣሥተ ው ለልዩ ፕሮግራም ሊሰጡ ቢችሉም፣ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን ቀጣይ አገልግሎት የሚሰጡት ላያኖራቸው ይችላል።

## አራተኛ ቀን፡- ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ሀ) ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሥራዎች የያዘ ዝርዝር ማዘጋጀት ጠቃሚ ሆኖ ማግኘት አለማግኘታችሁን ግለጹ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአመራር ሥራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል ከጊዜ አጠቃቀማቸው መቀየር ያለበት ነገር ምንድን ነው? ሐ) በመጀመሪያው ቀን ውስጥ የተመለከተውን ሠንጠረዥ በመመልከት ሁሉም ለው ሥራ ለሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ የአንድ ቀን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት ዝርዝር እንዲያዘጋጅ አድርጉ። መ) እንዲህ ዓይነቱ የጊዜ ሠሌዳ ሥራ ለሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ ምን ጥቅም እንደሚያስገኝ ግለጹ።

2. አብዛኞቹ መሪዎች የሚጠበቁባቸውን ሥራዎች ለማከናወን በቂ ጊዜ እንደሌላቸው በመግለጽ ያማርራሉ። ሀ) ብዙ ሥራን በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለ ማከናወን የተገለጹትን አሳቦች በመጠቀም ሥራ የሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ በአንድ ቀን ብዙ ሥራ

ሊያከናውን የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝሩ:: ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ኮሚቴዎች የሚሠሩበትን መንገድ በዚህ መጽሐፍ ለኮሚቴዎች አሠራር ከተሰጠው መመሪያ ጋር አነጻጽር:: ከእነዚህ መምሪያዎች/አሳቦች የምትስማማባቸውና የማትስማማባቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን? ሐ) እነዚህ መመሪያዎች ኮሚቴዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚሠሩበትን መንገድ እንዴት ሊለውጡ ይችላሉ?

3. ሀ) ነገሮችን ማዘግየት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ውጤታማነት የሚቀንሰው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎችን ጊዜ የሚያባክኑ ሌሎች ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

4. ሀ) ጥሩ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት አለመኖር በቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ችግር ሲፈጥር የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ዕዝራ መጀመሪያና በኋላ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ ገንዘቡን በሰ ዎች ፊት የቆጠረው ለምን ይመስልሃል? ይህ መሪዎች ለቤተ ክርስቲያኖቻቸው ጥሩ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋታቸው አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው?

5. ሀ) ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ከተገለጹት አጠቃላይ መርሖዎች የምትስማማባቸው የትኞቹ ናቸው? የማትስማማባቸውስ? ለምን? ለ) እነዚህ መርሖዎች አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አያያዝ ከሚያስቡት የሚለዩት እንዴት ነው? ሐ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ለአባሎቿ ስለ ገንዘብ፣ ስለ ዓላማውና በልግስና ስለ መስጠት የምታስተምረውን አሳብ ከልስ:: ቤተ ክርስቲያናችሁ እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ያለውን አመለካከት በተገቢው መንገድ እንድታስተምር ምን ቢደረግ መልካም ነው ትላለህ?



# ትምህርት አሥራ ስምንት

## አንደኛ ቀን

ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን መካከል ያለውን መተማመን የሚያከስመው ትልቁ ነገር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ የሚይዙበት መንገድ ሳይሆን አይቀርም:: ስለሆነም፣ ምእመናን ለእግዚአብሔር ሥራ እንድንጠቀምበት የሚሰጡትን ገንዘብ በፍጹም ታማኝነት ለአገልግሎት ማዋሉ ወሳኝ ነው:: በገንዘብ አጠቃቀማችን ዙሪያ ምእመናን እንዲያውቁ የማንፈልገው ነገር ካለ፣ ይህ የእግዚአብሔ ርን ገንዘብ በታማኝነት ያለመጠቀማችንን የሚያሳይ ነው:: አንድ ቀን የተደበቀው ነገር ይታወቅና መተማመን ይጠፋል:: አንድ ጊዜ ይህ መተማመን ከጠፋ ደግሞ፣ ለመሪዎች ይህንኑ መተማመን መልሶ ማግኘቱ ከባድ ነው:: ታማኞች ወይም ግልጾች ባለመሆናችን ምክንያት የእግዚአብሔር መንግሥት የተፈለገውን ያህል እንዳታድግ የሰይጣን መሣሪያ በመሆን እናገለግላለን:: ይህም የሚሆነው በታማኝነት ጉድለቱ ሳቢያ ምእመናን ገንዘብ መስጠታቸውን ስለሚያቆሙ ነው::

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መሪዎች በተሳሳተ የገንዘብ አያያዛቸው የሰይጣን መሣሪያ ዎች ሲሆኑ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በምሥጢራዊ መንገድ የሚይዙት ለምንድን ነው? ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር አለመሆኑን አብራራ::

**(ማስታወሻ፡- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎችን ብቻ እናብራራለን:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ትልቅ በምትሆንበት ጊዜ፣ በሂሳብ አያያዝ የሠለጠነ ሰው ብቃት ያለው የፋይናንስ ሥርዓት መመሥረት ይኖርበታል:: ከዚህ በታች የቀረቡት አሳቦች እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናችሁ ብቃት ያለው የፋይናንስ ሥርዓት እስከታዘጋጅ ድረስ ሊያገለግሉ የሚችሉ አሳቦች የሚገኙበት ነው:: የገንዘብ አስተ ዳደሩ የአንተ ሥራ ባይሆን እንኳን፣ ቤተ ክርስቲያን መልካም**